አማራ ኮሙኒኬሽን ቢሮ

# ሐዲስ



19ኛ ዓመት ቁጥር 65

መጋቢት ወር 2017 ዓ.ም



“የመንግሰት አገልግሎት አሰጣጥን ዘመናዊ፣ ፈጣንና ፍትሃዊ በማድረግ ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንፍታ”

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ

## ራዕይ

በመረጃ የበለፀገ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ በ2022 እውን ሆኖ ማየት

## Vision

To see a society with rich information and all rounded active participation for a better understanding on fundamental regional and country level affairs for having common consensus in 2030

## ተልዕኮ

በመንግስት ኮሙኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ መሪ ሚና በመጫወት በህብረተሰቡ መካከል ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በመሰረታዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዙሪያ የመላውን ህዝብ ግንዛቤ በማዳበር ሁለንተናዊ እድገታችንን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ለራዕያችን ስኬታማነት የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ፣

## Mission

playing a leading role in government communication information for a successful information exchange with in a society. to enhance the awareness of the people on the fundamental government policies strategies. plans and programs for a better step of succession our vision by stron collaboration.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየ 3 ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

የመጋቢት ወር 2017 ዓ.ም

19ኛ ዓመት ቁጥር 65

# ሐዱስ

**አዘጋጆች**

- ፍሬው ምናለ
- ይበልጣል መኮነን
- ሲሳይ ጌቴ
- ደፋሩ እምሬ
- ሳሮን ስማቸው

**አርታኢ**

- ጋርዳቸው አንሙት
- ፈቃዱ ገድፍ አስናቀ

**ህትመት ስርጭትና ክትትል**

- ደባሱ ካሣ

**ግራፊክስ ዲዛይን**

- ጌታሁን ላቀ

ገጽ

መልዕክቶች፡-

ደብዳቤዎች፡-

**ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር፡-**

በእጅ የያዙት ወርቅ. . . ......................................................07

**ልማት/ኢኮኖሚ፡-**

"እጅን በእጅ" ............................................................ 11

**ባህል/ ታሪክ፡-**


የማይሻር ብሔራዊ ክብር ................................................16

**ማህበራዊ፡-**

ትውልድ የማዳን ርብርብ .......................................... 20

**ልዩ ልዩ**

ዲጅታላይዜሽን ........................................................ 25



ውድ  አንባቢያን መጽሔታችንን በማንበብ  አስተያየታችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተሉት አድራሻዎቻችን ይላኩልን

Facebook- Amhara Communications

ኢሜል- anrsnproduction@ gmail. com

ዩቲዩብ- Amhara Communications

ቲውተር-    @ANRSGCAO

ዌብሳይት- www.amharacomm.gov.et

ስልክ-  058 220 09 40 ፤ 058 226 5921፣ 058 220 4107

ፋክስ-  058 220 1105 / 058 226 4172

ፖ.ሣ.ቁ      607

የዝግጅት ክፍሉ



የአብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን እና ተግባር መሰረት ለክልሉ ህዝብ የሚሰጠውን የመንግስት አገልግሎት አስመልክቶ ፖሊሲዎችን ፣ ሕጎችንና ደንቦችን ያመነጫል ፣ ያሻሽላል ፣ ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ለሚገኙ የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋ ፣ ውጤታማ እና ፍትሀዊ ሊያደረግ የሚችል ተቋማዊ ሪፎርም በመዘርጋት ምርትና ምርታማነት እንዲሻሻል የአንበሳውን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡ የተቋማትን አደረጃጀትና የስራ ስምሪት ውጤታማ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እያደረገ ነው፡፡

የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ የመንግሥት አገልግሎት እና አስተዳደርን በማሻሻል የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አመራሮችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የንቅናቄ መድረክ አካሂዶ ወደ ስራ ገብተናል፡፡ ኮሚሽኑ በስነ-ምግባሩ የተመሰገነ ፣ ነጻ ፤ ገለልተኛ ፤ ለዜጎች ቀልጣፋና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ መገንባት ስላለበት መጠነ ሰፊ ስራዎችን እየሰራ ያለ ነው፡፡

በመንግስት ተቋማትና ሰራተኞች የሚነሱ ቅሬታዎችን አስመልክቶ በክልሉ አራት የአስተዳደር ፍ/ቤት ምድብ ችሎቶችን በማቋቋም አስፈላጊውን ፍታዊ የሆነ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ስራዎችን አጠናክሮ እየሰራ ነው፡፡ ሀገራዊ ሪፎርሙን ተከትሎ በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎቶች ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጅ በመጠቀም ዲጅታላይዝ በማድረግለ ተገልጋዩ ተደራሽ እንዲሆን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እያከናወነ ነው፡፡ ሌላው ኮሚሽኑ በግብ ካስቀመጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ የሆነው ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር ሲሆን የመንግስት ሰራተኞች በሚሰሩበት አካባቢ የህጻናት ማቆያ ተገንብቶላቸው ልጆቻቸውን እየተንከባከቡ እገልግሎት እንዲሰጡ መመሪያ ከማዘጋጀት ባለፈ ኮሚሽኑ በግቢው ሞዴል የህጻናት ማቆያ ገንብቶ በማስመረቅ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በማህበራዊ አገልግሎቶች በመሳተፍ በባህርዳር ከተማ በችግር ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦችን በመደገፍና መኖሪያ ቤት ሰርቶ በማጠናቀቅ ከችግር መታደግ ችሏል፡፡

በመጨረሻም በክልላችን የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ዘመናዊ፣ ፈጣንና ፍትሃዊ በማድረግ ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንፍታ፡፡ ሁላችንም የክልላችን የመንግስት ተቋማትና ሰራተኞች የበኩላችን ድርሻ እንድንወጣ መልዕክት አስተላልፋለሁ፡፡

ወ/ሮ ባንቿአምላክ ገ/ማርያም

የአብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር



የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ድጋፍ አሰባሳቢና አስተባባሪ ምክር ቤት ጽ/ቤት በደንብ ቁጥር 82/2003 ዓ.ም የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት በአምስቱ የሕዝብ የድጋፍ ቀለበቶች ማለትም በፋይናንስ ፣ በጉልበት (በተፋሰስ ልማት) ፣ በሙያና በዕውቀት እንዲሁም በአመለካከት እና በዲፕሎማሲ ድጋፍ ባለፉት 14 ዓመታት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በያዝነው በጀት ዓመትም እንደዚሁ እስከ ሚያዚያ 30/2017 ዓ.ም ብቻ በጥሬ ገንዘብ ከመንግሥት ሠራተኞች ፣ ከባለሀብቱ ፣ ከንግዱ ኅብረተሰብ ፣ ከአርሶ አደሩ ፣ ከተቋማት ፣ ከድርጅቶች ፣ ከመያድ እና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በድምሩ ብር 88 ሚሊዮን 721 ሺህ 011.63 ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ በ14 ዓመት ጉዞ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ ብቻ አንድ ቢሊዮን 341 ሚሊዮን 822 ሺህ 274.01 ብር ተሰብስቧል፡፡ ከዚህም ባሻገር የህዳሴ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ እና ረዥም ዕድሜ እንዲያገለግል ታሳቢ ያደረገ የተፈጥሮ ሀብት ልማት እና ጥበቃ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በእዚህ እረገድ ግድብ ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን የተሰራው የተፋሰስ ልማት ሥራ በገንዘብ ሲተመን በድምሩ ብር 38 ቢሊዮን 595 ሺህ 388.00 አስተዋጽዖ መደረጉን ከክልላችን ግብርና ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት የኢትዮጵያዊያን የተፈጥሮ ሀብት በሆነው በአባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለና ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ፣ የብሔራዊ አርማና ኩራት ፣ የአሁኑ ትውልድ አሻራ ያረፈበት ፣ ለመጭው ትውልድ የሚተላለፍ የህልውና መሠረት የሆነ የዳግማዊ አድዋ ፕሮጀክት ነው፡፡ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ ሲቀመጥ የሀገራችን ሕዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ በአራቱም ማዕዘናት ደስታውን በመግለጽ ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ታሪክ ለመሥራትና ግድቡን ለማጠናቀቅ ቃል መግባቱ ይታወሳል፡፡ በገባውም ቃል መሠረትም ሁሉም ባለበት አካባቢና በየተሰማራበት የሙያና የሥራ መስክ በሚችለው አቅም እየተረባረበ ግንባታው አሁን ካለበት የመጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ብዙ ፈተናዎችን እያለፈ ግንባታው ለሰኮንድም ሳይቋረጥ እነሆ በሕዝብ ሁለንተናዊ የነቃ ተሳትፎ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅ 5,150 የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ ሲሆን ዓመታዊ የኃይል ምርቱ ደግሞ 15, 760 ጊጋ ዋት ይሆናል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ባሻገር የጤና እና የትምህርት ተደራሽነትን ያሰፋል ፣ የሕይወት ጥራትን ያሻሽላል ፣ ዘላቂ ልማትን ያመጣል ፣ በተጨማሪም በዓመት ከ10 ሺ ቶን በላይ ዓሳ ማምረት የሚያስችል ግድብ ነው። ከዚህም ባለፈ ግድቡ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ ስለሚይዝ የገጸ-ምድር የውኃ ሀብት ይጨምራል፡፡ ከ70 በላይ ደሴቶች እና ሰው ሠራሽ መስህብ ስለሚኖሩት ለቱሪዝም መስፋፋት የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡ ለአየር ንብረት መሻሻልም ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ ለቀጠናው ሀገራት በሁለንተናዊ ዘርፉ ትስስርን ያጠናክራል፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከውጥረት ይልቅ ትብብርን ፣ ከንትርክ ይልቅ ልማትን የሚያስቀድም የዳግማዊ አደዋ ፕሮጀክታችን ማሳያ ስለሆነ ግድቡ ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የነበረው ትብብራችን አሁንም በሁሉም አይነት ድጋፎች ተጠናክሮ እንዲቀጥል ስንል መልዕክት ለማስተላለፍ እንወደላን ሠላም፡፡

አቶ አባይነህ ጌጡ

የየአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ድጋፍ አሰባሳቢና አስተባባሪ ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ

# በእጅ የያዙት ወርቅ...

በሲሳይ ጌቴ

ሰላም በሕይወት ስንኖር ልናጣቸው ከማይገቡ ነገሮች የመጀመሪያው ነው፡፡ ሰላም የፍጥረታት ሁሉ የሕይወት መርህ ነው፡፡ ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው፡፡ በፍቅር ውስጥ ደግሞ ሰላም አለ፡፡ ሰላም የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ለማኅበራዊ ኑሮ መሠረቱ ሰላም ነው፡፡ ሰላምን በዋጋ መተመን ወይም በወርቅና በብር መግዛት አይቻልም፡፡

የሰላም ዋጋ ተመን የለውም፡፡ ፍጥረታት ሁሉ ሰላም ያስፈልጋቸዋል፤ ሁሉም ሰላምን ይሻሉ፡፡ ከየትኛውም ፍጥረት በላይ ለሰው ልጅ ደግሞ ሰላም ከምንም በላይ ነው፡፡ ሰላም ለሰው ልጅ የህልውና መሠረት ነው፡፡ ለህልውና አስፈላጊ የሚሆኑ ነገሮች ሁሉ በበቂ ሁኔታ ተሟልተው ፍጹም የሆነ መደላድል ተፈጥሮ ሰላም ባይኖር ከንቱ ነው፡፡

በአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ በተዘጋጀው መዝገበ ቃላት የሰላምን ፍች ከሌሎች የምስራቅ ሴማዊ ቋንቋ ቤተሰብ ስያሜ ጋር አያይዘው አቅርበውታል፡፡ ሰላም "በኩርስት (ሶሪያ ቋንቋ) ሽላም፣ በዕብራይስጥ (የእስራኤል ቋንቋ) ሻሎም፣ በአረብኛ ደግሞ ሰላም እንደሚባል እና ትርጉሙም ፍፁም ጤናን፣ ዕርቅን፣ ፍቅርንና አንድነትን፣ ደህንነትን፣ ተድላና ደስታን እንዲሁም ሰላምታን ያቀፈ ጽንሰሀሳብ ነው" ይሉታል፡፡ ሰላም "ሰው ሲገናኝ፣ ሲለያይ የሚለው፣ የሚናገረው ወይም የሚፈጥረው የቡራኬ የምርቃት ቃል ነው" ሲሉም ያክሉበታል፡፡

በቡድኖች፣ በማኅበረሰቦች፣ ከፍ ሲልም በሀገሮች መካከል የሚፈጠር ጠብ፣ አለመግባባት እና ግጭትን አጥፍቶ ሰላም ለማስፈን እልህ አስጨራሽ ትግል የሚደረገው የሰላም ዋጋ ተመን የማይወጣለት እጅጉን የላቀ ስለሆነ ነው፡፡ ሰላም እንዳናጣው ሁላችንም ተጠንቅቀን እና ተንከባክበን የምንጠብቀው ሲሆን እንደ አጋጣሚ ሆኖ በዙሪያችን ባሉ የሰላም አደፍራሽ ሁኔታዎች ምክንያት ካጣነው ሁላችንም በጋራ ጥረት ሠርተን የምንመልሰው መሆን አለበት፡፡

ሰላም ከምንም በላይ ስለሆነ ለሰላም ፍሊጋ የማይጓዙት ርቀት የማይወጡት ዳገት አይኖርም፡፡ ሰላምን በማኅበረሰብና በሀገር ደረጃ ለማስፈን የሚደረግ የማያቋርጥ ጥረት፣ የብዙኃን መገናኛ የፊት ገጾችን ከሚያጣብቡ ጉዳዮች መካከል ግንባር ቀደም ሆኖ የምንመለከተው ይኸው የሰላም ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሰላም በፊት ቅድሚያ የሚሰጥ ነገር ስለማይኖር ነው፡፡ የተረጋጋ ሰላም እንዲፈጠር ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እና የሰላም አደፍራሽ ሁኔታዎችን ቀድሞ መከላከል የሰላም መደፍረስን እና ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ዘርፈ-ብዙ ችግሮችን ለመከላከል እንደሚያስፈልግ በግልጽ የምንመለከተው ነው፡፡

የሁሉም መሰረት የሆነው ሰላም በኢትዮጵያዊያን በተለይም በአማራ ክልል ህዝብ ላይ ከራቀ ውሎ አድሯል፤ ዓመታም ተቆጥሯል፡፡ በህወኃት ጦርነት በከፍተኛ ሁኔታ ውድመትና ከፍተኛ ኪሳራ የደረሰበት ክልሉ በቅጡ ሳያገግም ለዳግም የእርስ በርስ ጦርነት ተዳርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት የክልሉ ኢኮኖሚ ተናግቷል፤ የህዝቡ ማህበራዊ መስተጋብር ተመሰቃቅሏል፤ በየቦታው ሞት፣ መፈናቀል እና ስደት ተበራክቶ ቆይቷል፡፡ አሁን ደግሞ በክልሉ ውስጥ በተፈጠረው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ቀውስ ፈጥሯል፡፡

ስለሆነም የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም በአማራ ክልል የተፈጠረውን ግጭት ለማስቆም እና የተፈጠረውን አንፃራዊ ሰላም በማስቀጠል እንዲሁም ወደ ተሟላ እና ዘላቂ ሰላም ለማሸጋገር እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በተመለከተ ከአማራ ክልል ሚሊሻ ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ (በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ) ከሆኑት ከአቶ ዳኛው በለጠ ጋር ቆይታ በማድረግ ያሰባሰብናቸውን መረጃዎች እንደሚከተለው አዘጋጅተናዋል፡፡ መልካ ንባብ፡፡

በአማራ ክልል ውስጥ የተፈጠረው ግጭት መነሻ ምክንያቶች በርካታ ናቸው፡፡ ለአብነት እንኳ ብንጠቅስ አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በወቅቱ መፍታት አለመቻሉ ነው፡፡ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ በገንዘብ መሸጡ የክልሉን ማህበረሰብ ጥያቄ ከማንሳት አልፎ በመንግስትና በህዝብ መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ከፍተኛ የስራ አጥነት ቁጥር መኖሩና የኑሮ ውድነቱ በራሱ በህዝቡ ላይ ያስከተለው ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ ህዝቡን ወደ ስሜት ውስጥ እንዲገባ ገፋፍቶታል፡፡ የክልሉን ማህበረሰብ ስሜት በመረዳት ህገ-ወጡ ቡድንም ይህንን እንደ መቀስቀሻ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡

የፍትህ ተቋማት ላይ ህብረተሰቡ እምነት ማጣቱ እና ፍትህ በተዛባ መንገድ በገንዘብና በሙስና መሸጡ፣ ህገ-ወጥ ደላላ መልክ አለመያዙ እና ለሚነሱ የፍህ አገልግሎት ላይ የተዛባ አመለካከት መፈጠሩ ሌላኛው የግጭት መነሻ ሆኗል፡፡

የህዝቡን ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅ አለመቻል፣ ስርቆት፣ ግድያ፣ እና ልዩ ልዩ ወንጀሎችን ማስቆም አለመቻሉ፣የተለያዩ ህገ-ወጥ ጦር መሳሪያዎች በግለሰቦች እጅ መኖሩ፣ለተፈጠረው ቀውስ እንደ አባባሽ ምክንያት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ለአርሶ አደሩ የሚቀርቡ የግብአት አይነቶች ማለትም የአፈር ማዳበሪያ እና ምርጥ ዘር ለታለመለት አላማና ግብ ወቅቱን በጠበቀ መንገድ ለአርሶ አደሩ መቅረብ ሲገባው በህገ-ወጥ ነጋዴ ቁጥጥር ስር እየዋለ ህዝቡ ላይ የዋጋ ጫና ፈጥሯል፡፡




"ሰላም ለሁሉም ነገር መሰረት ነው"

ዋናዎቹ ለግጭቱ መነሻ ምክንያት ከሆኑት መካከል የክልሉ ህዝብ የሚያነሳቸው የመብት ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ ባለመሰጠቱ ምክንያት ነው፡፡ ከእነዚህ ጥያቄዎች መካከል የሰብአዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች ላይ ተገቢ የሆነ ምላሽ አለመስጠት ነው፡፡

የአጎራባች ክልሎች ጣልቃ ገብነት በተለይ የህወሓት ጦርነትና መሰል ጉዳዮች በክልሉ ውስጥ እጃቸውን አስገብተው መስራታቸው፣ የተዛባ እና ስሁት ትርክት በህዝቡ ላይ የፈጠረው የስነልቦና ጫና ያሳደረ መሆኑ ለተፈጠረው ግጭት መነሻ ሆኗል፡፡

የህገ-መንግስት ማሻሻያ ጥያቄዎች ምላሽ አለማግኘት፣ የአማራ ህዝብ በመላው ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ የሚኖር እንደመሆኑ መጠን መብቱ እንዲከበር ባለመደረጉ እንደ አንድ ማሳያ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ የተነሳ የሚደርሱ የመብት ጥሰቶች በመኖራቸውና የስደትና የመፈናቀል መጠኑ በእጅጉ በመበራከቱ ምክንያት ነው፡፡

ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የማህበራዊ ሚዲያ ሃሰተኛ ፕሮፓጋንዳ በህብረተሰቡ ዘንድ የበላይነት በመያዙ ህዝቡን በስሜት ኮርኳሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን በመጠቀም የሃሰተኛ ወሬ መብዛትና በዚህ ላይም ህብረተሰቡ ሰለባ መሆኑ እና ይህን ሊመክት የሚችል የመንግስት ሚዲያ ሽፋን ውስን በመሆኑ ምክንያት በክልሉ ለተፈጠረው ግጭት የበኩላቸውን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ ክልሉንም ወደተራዘመ ጦርንት ውስጥ በማስገባት ኢኮኖሚያዊ፣ ሰብዓዊና ማህበራዊ ኪሳራ እንዲደርስ አድርገዋል፡፡

እንደዚህ አይነት መሰል ችግሮች የገጠማቸው ሃገራት በተለያየ መንገድ መፍታት ችለዋል፡፡ የአማራ ክልል ደግሞ አሁን ካለበት ሁኔታ ለመውጣት እንደአማራጭ መውሰድ ከሚገባው የችግር መፍቻ መንገዶች መካከል የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በወቅቱ ምላሽ በመስጠት ሰላምና ልማትን ቅድሚያ የሚሰጥ የትግል ስልት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ቁርጠኛ የሆነ አመራርና በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመራር በማደራጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን በአግባቡ በመስራት በጠረጴዛ ዙሪያ ችግሮችን አቅርቦ በውይይት መፍታትና መተማመንን በመፍጠር የተፈጠሩ ችግሮችን ለመቀልበስ ያስችላል፡፡

የስራ እድል ፈጠራን አጠናክሮ በመቀጠል ወጣቱን የስራ እድል እንዲያገኝ በማድረግ እንዲሁም የህግ የበላይነትን በአግባቡ በማስከበር የህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን በማስቆምና አቅርቦትን ማሳደግ ይገባል፡፡ አባባሽ ምክንያት የሆነውን ኑሮ ውድነትን ለመግታት የማዳበሪያና የምርጥ ዘር፣አቅርቦትን በስፋት በማዳረስ በግጭት የተወጠረውን ማህበረሰብ በማነቃቃት ወደ ልማት በማስገባት ሰላም እንዲሰፍን መስራት ያስፈልጋል፡፡

የዜጎች መብት ሰብዓዊ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች እንዲሁም ህገ-መንግስታዊ የመዘዋወር ነፃነቶችን እንዲከበር ማድረግና ማፈናቀልን በማስቆም የክልሉን ሁለንተናዊ ሰላም ማስጠበቅና ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሚሊሻ ጽፈት ቤት ከሌሎች ሰላም ሊያስከብሩ ከሚችሉ ተቋማት ጋር በመተባበርና ግንባር ቀደም ኃላፊነት በመውሰድ ሰላም ለማስፈን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡


ክልሉ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለወራት ሲተዳደር ቆይቷል፡፡ ይህ መሆኑ ክልሉን በብዙ መልኩ ከተለያዩ ስጋቶችና ተደቅነው ከነበሩ ጉዳቶች ለመከላከል ተችሏል፡፡ ለአብነትም ክልሉ እንዳይፈርስ ከፍተኛ እገዛ ከማድረግ በሻገር ህዝቡ እንዳይጎዳ የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ህገ-ወጥ ታጣቂ ሃይሉን መልክ ለማስያዝ ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በከተማም ይሁን በገጠር ከፀጥታ ኃይል ውጭ ጦር መሳሪያ ይዞ መዘዋወር እንደሌለበት በመደረጉ ምክንያት ስርቆት፣ ውንብድና እና ግድያ እንዳይስፋፋ አግዟል፡፡

የክልሉ ልማት ከዚህ በላይ እንዳይጎዳ እና የመንግስት መዋቅር መልሶ እንዲደራጅ እንዲሁም የክልሉን የጸጥታ መዋቅር እንዲጠናከር በተለይ ህብረተሰቡ ባደረገው ድጋፍ በስልጠና እና በሎጀስቲክስ ድጋፍ በማድረጉ ራሱን ችሎ እንዲጠናከርና በክልሉ መዋቅር ሰላሙን ማስጠበቅ እንዲቻል የክልሉ ሚሊሻ ጽህፈት ቤት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

የመንግስት ተቀዳሚ ሃላፊነቱ የዜጎችን ደህንነት ማረጋገጥና የህግ የበላይነት እንዲከበር ማድረግ ነው፡፡ የዜጎችን መብት ለማክበርና ለማስከበር ደግሞ የተለያዩ ተቋማት በክልሉ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የአማራ ክልል ሚሊሻ ጽህፈት ቤት በክልሉ ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት ወደከፋ ሁኔታ እንዳይሸጋገር እና በከፍተኛ ሁኔታ የተባባሰ ቀውስ እንዳይፈጠር የሚጠበቅበትን ተግባርና ሃላፊነት በአግባቡ እያከናወነ ይገኛል፡፡

የክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት በአዋጅ ሲቋቋም የተሰጠው ተልዕኮ ህግ የማስከበር ተግባር በመሆኑ ይህንን በአግባቡ ለመወጣትና የህግ የበላይነት እንዲከበር

# ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር




*“ግጭት የውድመት ሰላም ደግሞ የእድገት መሰረት ነው!”*

የራሱን ሚና ለመወጣት ብዙ መስዋትነትን በመክፈል በርካታ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ በርካታ በክልሉ አካባቢ ያለው ህገወጥ ታጣቂ ቡድን ይዞት የነበረውን ወረዳና ቀበሌ ነጻ በማድረግ የመንግስትን መዋቅር ለመዘርጋት ከበርካታ የህይወት መስዕዋትነትና የአካል ጉዳት፣ የሀብትና ንብረት ውድመት እንዲሁም የፀጥታ ሀይሉ ቤተሰቦች ላይ ጉዳት መድረስን ተቋቁሞ ህግ እያስከበረ ይገኛል፡፡

ከሰሜኑ ጦርንት መጠናቀቅ ተያይዞ ተበትኖ የነበረውን የጸጥታ መዋቅር አሁን ድረስ በአዲስ እያሰባሰበ፣ እያሰለጠነ እና በአዲስ መልክ በማደራጀት ህግ እንዲከበር እያሰማራ የክልሉን ሰላም ወደነበረበት እንዲመለስ ከፍተኛ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በህግ ማስከበር ዘመቻ የተሰባሰበው ሚሊሻ እየደረሰበት ያለውን ጫናን ተቋቁሞ ህግ የማስከበር ስራውን እየተወጣ ነው፡፡ በተጨማሪም በክረምትም ሆነ በበጋ ወራት የታጠቁ ኃይሎች ህግ እንዲያስከብሩ የተጠረነፉ የሚሊሻ አባላትን የእርሻ ማሳቸውን ህብረተሰቡ ተባብሮ በዘር እንዳይሸፍንላቸውና የአረም ስራ እንዳይሰራላቸው በማድረግ የማሸማቀቅ ስራ ቢሰራም ይህን ሁሉ ተቋቁመው እንዲሰሩ የስነ ልቦና ግንባታ በመስጠት ህግ የማስከበር ስራ እንዲሰሩ የማድረግ ስራ በተቋሙ በኩል እየተሰራ ይገኛል፡፡

ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በመጠበቅ የሕዝቡን ሰላም ለማረጋገጥ የሚችሉ አዳዲስ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት የመመልመል እንዲሁም ነባር የሚሊሻ አባላትን ጨምሮ ፓለቲካዊና ወታደራዊ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት አደራጅቶ አስፈላጊውን ትጥቅ በማስታጠቅ የህግ ማስከበር ስራዎችን በትኩረት እየሰራ ነው፡፡ ለአብነት ህዝብን ለስቃይና እንግልት እየዳረገው ያለው ህገ-ወጥ ኃይል ላይ አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ የህዝቡን ሃብትና ንብረት እንዲሁም ደህንነት በመጠበቅ አስፈላጊውን መስዋትነት እየከፈለ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የመንግስትም ሆነ የግለሰብ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ጉዳት እንዳይደርስባቸው የመጠበቅና የመከላከል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

አሁን ላይም ግጭት ባለበት አካባቢ ሕይወት እንዳይጠፋ እና ንብረት እንዳይወድም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረተ ይገኛል፡፡ የመንግስት የጸጥታ መዋቅር ሰላማዊ ዜጎች እንዳይጎዱ ብርቱ ጥንቃቄ በማድረግ የከፋ ችግር በንፁሃን ዜጎች ላይ እንዳይደርስ እተከላከለ ነው፡፡ በውጤቱም በህዝቡ ዘንድ የተዛባውን አመለካከት እንዲያስተካክል እና ለመንግስት ሃይል ድጋፍ እንዲያደርግ በተዛባ መንገድ ተደናግሮ ወደተሳሳተ መንገድ የገባውን ማህበረሰብ ወደ ቀልቡ የመመለስና የማደራጀት ስራ እያከናወነ ነው፡፡

በክልሉ ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት በአጭሩ ለማስቆም እንደ ክልል የተሰሩ ስራዎች ከፍተኛ ለውጥ አምጥተዋል፡፡ ለአብነትም ግጭቱን ለማስቆም ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ግንኙነት ስራ በመስራት እውነቱን ለማስረዳት በተደረገው ስራ ህገወጥ ቡድኑን ከህዝብ ለመነጠል ተችሏል፡፡ ህገወጥ ታጣቂው ህዝብን ከፊት እያሰለፈ በማደናገር ያደርገው የነበረውን ሕዝባዊ መልክ የመቀነስ ስራ በመስራት እንዲሁም የውስጥን አቅም በማጠናከር ጥምር ሃይል በመፍጠር ጠላትን በግልጽ ለመፋለም ህዝቡን ነጻ በማውጣት ላይ ነው፡፡

ተደናግረው ወደ ትግል የገቡትን ህገወጥ ቡድኖች በማወያየት ወደ ሰላም አማራጭ እንዲመጡ ተሃድሶ በመስጠት ድጋፍ በማድረግ ወደ ህብረተሰቡ ተቀላቅለዋል፡፡ ይህ በመደረጉ ክልሉ ተረጋግቶ እንዲቀጥል አስችሏል፡፡ የተቋረጡ የልማት እንቅስቃሴዎች እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡ የሰለጠነው የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባላት በየወረዳው ከጥምር ጦሩ ጋር በማሰለፍ የአካባቢውን ማህበረሰብ በማወያየት ራሱን በራሱ ህግ እንዲያስከብር የማስገንዘብ ስራ በመስራት በርካታው የክልሉ ከተሞችና ቀበሌዎች ከጠላት ነጻ መሆን ችለዋል፡፡ የመንግስት መዋቅር መዘርጋትና ህዝቡን ለማስተዳደር ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

የድጋፍና ክትትል ስራው ከክልል ጀምሮ በተቀናጀ መንገድ እስከ ወረዳ ድረስ የአካል ድጋፍ በማድረግ የተሻሉና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ሚሊሻዎች በማስመልመል አቅማቸውን ለማጎልበት የሚያስችል የስልጠና ድጋፍ በማድረግ ሃይል ማሰባሰብ እና ማደራጀት ተችሏል፡፡ ከዚህ አንፃር በራስ አቅም የክልሉን ሰላም ለማስከበር የሚያስችል ስራ በማከናወን ህዝቡን ከመንግስት ጎን እንዲቆም ሆኗል፡፡ የጠላትን እኩይ አላማ ለህዝቡ ማስረዳት በመቻሉ የጠላት ድጋፍ ቀንሷል፣ የሎጅስቲክ መሰረቱን አጥቷል፣ ጠላት ቁሞ እንዳይዋጋና አቅም እንዲያንሰው የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

በክልሉ የተፈጠረውን ግጭት ለማስቆም የሕብረተሰቡ፣ የሃይማኖት አባቶች እና የሃገር



"ሁሉም ለሰላም እጁን ሊዘረጋ ይገባል"

ሽማግሌዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ለአብነትም ህብረተሰቡ ጠላት እንደማይጠቀመው በመገንዘብ ወደ ራሱ ተመልሶ መንግስትን እየደገፉ አካባቢውን እያስጠበቀ፣ ተደራጅቶ እየሰለጠነ እና ለመንግስት ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡ የሃይማኖት አባቶች ምእመናኑን በማስተማር የታጠቀ ሃይል ወደ ሰላም እንዲመጣ የማድረግ ለሰላምና ለህግ የበላይት መረጋገጥ የድርሻቸውን እየተወጡ ነው፡፡

የሃገር ሽማግሌዎች ደግሞ በህገ-ወጥነት ታጥቀው ጫካ የገቡ ሃይሎችን ዋጋ እየከፈሉ ጭምር ወደ ሰላም እንዲመጡ በማድረግ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እየተወጡ እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እየሰሩ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ህብረተሰቡ፣ የህይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ህገ-ወጥ ታጣቂው እጁን ለመንግስት እንዲሰጥ የማድረግ ስራ በመስራት እና በየቀኑ የታዩ ለውጦችን ከቦታ ቦታ በተሞክሮነት የማስተላለፍ ስራ እሰራ እያከናወነ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ክልሉ ከነበረበት ቀውስ ወጥቶ ወደ አንፃራዊ ሰላም እየመጣ ነው፡፡

የተፈጠረውን አንፃራዊ ሰላም አጽንቶ ለማስቀጠል እና ወደ ተሟላ ሰላም ለማሸጋገር እንዲሁም የማህበረሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ህብረተሰቡን በማወያየት የሰላሙ ባለቤት እንዲሆን በማድረግ የተደራጀና ጠንካራ አመራር በመፍጠር ህዝቡን ታች ወርዶ በመደገፍ ላይ ነው፡፡ የተጠናከረ ሃይል የማሰባሰብ ስራ በመስራት የራሱን ጸጥታ ከህዝቡ ጋር ሆኖ የሚጠብቅ ራሱን የቻሉ ሃይል የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

በመንግስት በኩል የሰላምን አማራጭ በመከተል ህገ -ወጥ ታጣቂ ሃይሉን ወደ ድርድር እና ውይይት ሊያመጡ የሚችሉ አጀንዳዎችን አሟጦ የመጠቀም ስልትን ይመከራል፡፡ ምክረ ኃሳቡን ተጠቅመው ውጤት ሲገኝ  የተገኙ ውጤቶችን ተሞክሮችን ሌሎች እንዲጠቀሙበት ያስተላልፋል፡፡ በዘላቂነት ሁሉን አቀፍ ሰላም እንዲመጣ የውይይት አማራጮችን በተሟላ መንገድ በመጠቀም የታጠቀውን ሃይል ወደ ሰላም የመመለስ ስራ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲሰራ ማስገንዘብ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ውጭ ያለውን ሃይል ህግ በማስከበርና የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ ሰላሙን ማስቀጠል እንዲሁም የማያቋርጥ የህዝብ ግንኙነት ስራ በእውነት ላይ ተመስርቶ ለህዝቡ መረጃ በመስጠት የማስገንዘብ ስራ እያከናወነ ነው፡፡

ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የሰላም አማራጮችን አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የሌሎች ሃገራትን ተሞክሮ ለክልሉ ማህበረሰብ እንዲሁም ለታጣቂ ቡድኑ እና ለሌሎች አካላት በማስገንዘብ ለውይይትና ለድርድር በርን ክፍት በማድረግ ዘላቂ መፍትሄ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

በአማራ ክልል የተገኘውን አንፃራዊ ሰላምን አጽንቶ ለማስቀጠል እያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ህዝባዊ ሃለፊነቶችን ሊወጡ ይገባል፡፡ ለአብነትም ማህበረሰባችን፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የመንግስት አመራሩና ሰራተኛው፣ ወጣቶች፣ ሴቶች በየዘርፉ የራሳቸውን ሰላም በራሳቸው እንዲያስከብሩ በማድረግ ይህን አንጻራዊ ሰላም አጠናክሮ በማስቀጠል ወደ ተሟላ ሰላም ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡ሃገር በቀል የሲቪክ ማህበረሰብ ድረጅቶችም ማህበረሰቡን በማንቃት፣ታጣቂ ቡድኑን ወደ ድርድርና ሰላም እንዲመጣ የማስረዳትና የመጎትጎት ስራ ሊሰሩ ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ዳኛው መንግስት የሰጠውን የምህረት አዋጅ በመጠቀም ወደ ጫካ የወጡ ወንድሞችን በማወያየት ወደነበሩበት ቦታቸው እንዲመለሱ የማድረግ ስራውን አጠናክሮ ማስቀጠል ይኖርበታል፡፡ ሁሌም የሰላም አማራጮችን በየጊዜው በመጠቀም የህይወት መጥፋት፣ የንበርት ውድመት፣ የኢኮኖሚ ድቀትና ማህበረዊ ምስቅልቅል ወደከፋ ደረጃ እንዳይደረስ በማድረግ የክልሉን ህብረተሰብ ደህንነት ማስጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ለሰላም መስፈን የሁሉም ዜጋ ድረሻ ያለው ስለሆነ ተልዕኮውን ይዞ በትኩረት መስራት ይኖርብታል በማለት ሃሳባቸውን አካፍለውናል፡፡

የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም አቶ ዳኛው በለጠን ስለሰጡት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ እያመሰገን "በእጅ የያዙት ወርቅ ከብረት እኩል ነው" እንደሚሉት አበው በክልሉ ውስጥ የተፈጠረውን የእርስ በርስ ጦርነት እያደረሰ ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ሰብዓዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሁሉን አቀፍ ምስቅልቅልና ጉዳት ክልሉን ወደ ኋላ እየጎተተው መሆኑን በመረዳት ከግጭት ይልቅ ሰላምን፣ ከመገፋፋት ይልቅ መተሳሰብን ታሳቢ በማድረግ የእርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከር ሁሉም ለአንድ አላማ በመቆም ለክልሉ ህዝብ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ፖለቲካዊ የበላይነት፣ ማህበራዊ መስተጋበር እና ድህነትን በመፋለም የክልሉን ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ለመገንባትና ለማረጋገጥ ለሰላም መስፈን ቅድሚያ መስጠት ይገባል በማለት መልዕክቱን ያስተላላፋል፡፡ ሰላም!!!

# "እጅን በእጅ"

በይበልጣል መኮንን

ተፈጥሮና የሰው ልጅ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በጋራ መስተጋብር መኖራቸው እሙን ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይህን የተፈጥሮ ግዴታ በአግባቡ መጠቀም አልቻሉም፡፡ ለእዚህ ማሳያ ደግሞ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ጦርነት ማወጁ ነው። ሰው ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር አውላለው በሚለው መሰረተቢስ ቅዥትና ከጣራ በላይ ፍላጎት በራሱ ላይ ቅጣትን አውርዶ የችግሩ ገፈት ቀማሽነቱን እንዳስጠበቀ ነው፡፡ የሰው እና የተፈጥሮ ጦርነት ውሎ ያደረ ቢሆንም አሁን ባለንበት ዘመንም ጠቡ ተባብሶ መቀጠሉን በዙሪያችን ያለውን አካባቢ መቃኘት በቂ ነው፡፡ ለእዚህ ደግሞ "ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል" እንደሚባለው ሁሉ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ባለው መስተጋብር ተፈጥሮ አምርራ ከመቀየሟ የተነሳ የሰው ልጅ ላይ ፊቷን ያዞረችበት ከባድ ወቅት ለመሆኑ ብዙ መገለጫዎችን ማንሳት እንችላለን፡፡ ለእዚህም ነው ተፈጥሮ ላይ እያደረሰ ያለው ዘርፈ ብዙ ፈተና ምስክር አያስፈልገውም የሚባለው፡፡

አሁን ላይ በዓለም አካባቢ የሚነሱ የተፈጥሮ ቀውሶች ሁሉ መነሻቸው የሰው ልጅ ነው ከሚል ድምዳሜ መድረስም ተችሏል፡፡ ጥንቃቄ የጎደለው የሰዎች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ላይ እያደረሰ ያለው ከጊዜ ወደ ጊዜ የችግሩን መጠን ከፍ እያደረገው መጥቷል፡፡ ለማሳያነትም የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ከባድ ዝናብና ጎርፍ፣ የመሬት ናዳ ፣ ከባድ ቅዝቃዜና በረዶ ፣ ከባድ ሙቀትና ድርቅ ፣ ሰደድ እሳት፣ እሳተ ጎሞራ እያልን የምንዘረዝራቸው የተፈጥሮ አደጋዎች መነሻቸውም ሆነ መድረሻቸው ይህው የሰው ልጅ ነው።

ወደ ሀገራችን ስንመጣ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች አገር ስትሆን ተስማሚ አየር እና ለምለም ምድር ባለቤት ናት፡፡ ኢትዮጵያ ብዙ የተለያዩ ሥርዓተ-ምኅዳር ያላት ሀገር ስትሆን በዚህም ምክንያት በአዝርዕት እና ብዝኃ-ሕይወት የከበረች መሆኗ ግልፅ ነው፡፡ ይህም ጉዳይ ኢትዮጵያን በዓለም ደረጃ "የብዝኃ-ሕይወት ማዕከል" ደረጃ ውስጥ አስገብቷታል፡፡

ይሁን እንጅ በአሁኑ ሰዓት ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ የተራቆተ እና የተጎሳቆለ መሬትን የያዘች ሀገር ስትሆን እንደ ክልልም አማራ ክልል አንዱ ነው፡፡ አማራ ክልል ከኢትዮጵያ 15 በመቶውን የሚሸፍን ሰፊ ክልል ሲሆን ክልሉ በበርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች የታደለ፣ የተለያዩ የአየር ንብረት ቀጠናዎች ባለቤት ፣ ማራኪ መልካምድር ፣ የበዙ የውሃ ሀብቶች እንዲሁም የተለያዩ የብዛ ህይዎት መኖሪያም ነው፡፡

ነገር ግን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ በመጣውና አሁን ባለው ግዴለሽ በሆነ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም የክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት እየደረሰበት መምጣቱ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም እንደ ክልል እየተመናመነ የመጣውን የደን ሽፋን መልሶ ለማሳደግና የአገሪቷን የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ ስራ በኩል ምን እየተሰራ ነው? ፣ ምንስ ጎደለ? የተገኙ ስኬቶችስ ምንድን ናቸው? የሚሉትንና  መሰል ተፈጥሮ ሀብትን በማልማት ፣ በመጠበቅ እና በመንከባከብ በኩል ምን ተሰራ ምን ጎደለ የሚሉትን በርካታ ጥያቄዎችን  ሐዲስ መጽሄት አካታ ከዘርፉ ባለሙያ ጋር ያደረገችውን ቆይታ እንካችሁ ትላለች መልካም ንባብ፡፡

አቶ እስመለዓለም ምሕረቱ በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ አቶ እስመለዓለም እንደሚሉት በሀገራችን የተፈጥሮ ሀብት ልማት በ1960 ዎቹ መጨረሻ እና በ1970 ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ እንደተጀመረና የአጀማመሩም መነሻ ሀሳብ በምስራቁ አካባቢ ከፍተኛ ድርቅ በመከሰቱ የተነሳ ድርቁን ለመታደግ ሲባል እንደተጀመረ ያስረዳሉ፡፡

ምክንያቱም ደግሞ በአካባቢው የሚኖሩ ህዝቦች የደን ሽፋንን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይጠቀሙበት ስለነበር የደን መመናመን በመከሰቱ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአካባቢው ምርት በመቀነሱ ህዝቡን ለመታደግ የግድ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ አስፈላጊ ነበር፡፡

የአካባቢ ልማት ፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ ዋና እሳቤ የነበረውም በድርቅ ምክንያት ተቸግሮ የነበረውን የምስራቁን አካባቢ ማህበረሰብ ወደ ሌላ አካባቢ ሳይፈናቀል መመገብ  ስለነበረበት ተፈጥሮን አልምቶ እንዲመገብ ታሳቢ ተደርጎ የተጀመረ ነው፡፡

በእርግጥ አጀማመሩ በወቅቱ በርሀብ ውስጥ የነበረውን ህዝብ በቀጥታ የተፈጥሮ ሀብት ልማት እንዲሰራ ሳይሆን የእርዳታ እህል እንዲቀርብለትና ከችግሩ እንዲያገግም ነበር የተደረገው፡፡ ቀስ በቀስ ግን የእርዳታ እህሉን እተጠቀመ እገረመንገዱንም የተጎዳውን የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት በማልማት እንዲጠቀም ተደርጓል፡፡ ይህም የልማት ስራ የእርዳታው ማግኛ ግዴታ ስለነበር "ምግብ ለሥራ" እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የተፈጥሮ ሀብት ስራውን ዘላቂ ከማድረግ ጎን ለጎን በርካታ ስራዎች እየተሰሩ በመምጣታቸው 1980 ዎቹ አካባቢ በአጭር ጊዜ ታቅደው የሚሰሩ የልማት ስራዎችን ታሳቢ ያደረገ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ ተጀመረ፡፡ የሚሰጠው ተግባር የአጭር ጊዜ እቅድ የሚፈፀም ስለነበር መንግስት ህብረተሰቡን እየመገበ አጫጭር የአካባቢ ልማት ስራዎችን የማሰራት እሳቤ በውቅቱ በነበረው ፕሮግራም ሲተገበር ቆየ፡፡

እንደነዚህ አይነት የአጭር ጊዜ እቅዶች ቀስ በቀስ ዘላቂ በሆነ መልኩ እንዲሰሩ ተደረገ፡፡ ከእነዚህ በዘላቂነት ከተሰሩ ስራዎች መካከል ከቆቦ እስከ ሸዋ ሮቢት ያለውን አካባቢ በደን መሸፈን መቻሉ በወቅቱ የተመዘገበ ትልቅ ስኬት ነበር፡፡ በእዚህ አካባቢ የተገኘው ውጤት በፍጥነት ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲዛመት በመደረጉ የክልሉን በርካታ ተራራማና ጉርጅ ቦታዎችን በደን መሸፈን

# ልማት/ኢኮኖሚ



አቶ እስመለዓለም ምሕረቱ
የተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የተቻለበት ወቅት ነበር፡፡ የተገኘው ውጤትም ለበርካታ ዓመታት ከህብረሰቡ ጋር ያለሰለሰ ጥረት በመደረጉ የተገኘ ስኬት ነበር፡፡ በተሰራው ስራ ውሃዎችን ማግኘት ተችሏል፡፡ በርካታ ምንጮች ጉልብተዋል፡፡ ህብረተሰቡም በእነዚህ በተገኙ አመርቂ ውጤቶች ተነቃቅቶ የአካባቢ ተፈጥሮ ሀብትን የመጠበቅ እና የመንከባከብ ግንዛቤው በእጅጉ እያደገ መጣ፡፡

በእዚህ ልክ የተገኘው ግንዛቤ እንደመነሻ ሀሳብ ተወስዶ በ1990 ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሀገር አቀፍ መመሪያ ተዘጋጀ፡፡ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት እቅድ ከላይ ወደታች መውረዱ ቀርቶ ከታች ወደ ላይ እንዲታቀድ ተደረገ፡፡ በተሰጠው አቅጣጫ ህብረተሰቡ ተስማምቶ በሁሉም አካላት ሊተገበር የሚችል የስራ ክፍፍል ተደረጎ ወደ ስራ ተገባ፡፡

በተደረገው ንቅናቄ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ እና አጠቃቀም ስራ የተፈጥሮ ሀብቱን ብቻ አልምቶ የሚቆም ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሁለንተናዊ ልማት እንዲያመጣ ተደርጎ በውይይት የዳበረ የተግባር ስራ ሲሰራ ቆየ፡፡

በትግበራ ስራው የመጀመሪያው ዙር ትኩረት አቅጣጫ የነበረው ሥነ- አካላዊ ስራው ላይ ብቻ ነበር፡፡ በኋላ ላይ በሥነ- አካላዊው ብቻ መወሰን አካባቢን መቀየር እንደማይቻል እና የአፈር ክለት በሚፈለገው መልኩ መቀነስ እንደማያስችል ግንዛቤ ተወስዶ ሥነ-ህይዎታዊ ስራው አብሮ ጎን ለጎን እንዲሰራ ሁኔታዎች ተመቻቹ፡፡ በተሰራው ስራ በአጭር ጊዜ ለገበያ የሚውሉትንና ሌሎች ሰብሎች እንደየ አካባቢው ሁኔታ እየተለዩ የተተከሉበት ወቅት ሲሆን በሁሉም አካባቢ በሚባል ደረጃ ደግሞ የእንስሳት መኖ በስፋት እንዲተከል ተደርጎ ውጤት የተመዘገበበት ወቅት ነበር፡፡

የአፈር ክለትን በመቀነስ በየአመቱ እየታጠበ ይሄድ የነበረውን ለም አፈር በማስቀረት ለምነቱ እንዲጨምር የማድረግ ስራዎች በስፋት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በተለይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የገፀ-ምድር እና ከርሰ-ምድር ውሃ የማበልጸግ ስራ ተሰርቷል፡፡ እነዚህ የተገኙ ውጤቶች የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራው ይበልጥ ዘላቂነቱ እየተረጋገጠ መምጣቱን ማመላከት ቻሉ፡፡

የተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ይበልጥ ለማረጋገጥ ሲባል ካሽ ክሮፕን በተለያዩ አካባቢዎች ከመትከል ባለፈ ፣ በንብ ማነብ ፣ በፍራፍሬ ተክል ፣ በእንስሳት መኖ ፣ በከብት ድልብ እና በተለያዩ ተግባራት እንዲሰማሩ በማድረግ በኩል የተሰራው ንድፈ ሀሳብ ወደ ተግባር ተቀይሮ በርካታ ውጤቶች ተመዝግበውበታል፡፡ ተጠናክሮ የቀጠለው ይህ እንቅስቃሴ የተፋሰሶችን ቁጥር እያሳደገ ስለመጣ ተጠቃሚነታቸውንም በዛው ልክ ማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት ማከናወን ተችሏል፡በእዚህ ልክ እየጠነከረ የመጣውን የተፋሰሶችን ግንዛቤ ይበልጥ ለማሳደግና ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ከህብረት ስራ ማህበራት ጋር በተደረገ የቅንጅት ስራ ተፋሰሶች ህጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከህብረት ስራ ማህበራት ጋር በተሰራው የቅንጅት ስራ የለሙ እና ወደፊት የሚለሙ ተፋሰሶች በማለት ተለይተው ህጋዊ ሰውነት ኑሯቸው እንዲቋቋሙ ተደርገዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓትም በክልሉ ከሶስት ሽህ ዘጠኝ መቶ በላይ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ተፋሰሶች አሉ፡፡ እነዚህ ተፋሰሶች የራሳቸው የሆነ የገቢና ወጭ ማዘዥያ ያላቸው ናቸው፡፡ የመክሰስ እና የመከሰስ መብታቸው ሙሉ በሙሉ ተረጋግጦላቸው ስራላይ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ ብድር የማበደር የበመደረ እና ብድሩን የማስመለስ ሙሉ መብት ያላቸው ሲሆኑ እነዚህ ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው ተፋሰሶች ቅሬታ ሲኖራቸው ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት በእራሳቸው የተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ አባላት ያላቸው ናቸው፡፡

እያደገ የመጣው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ስራ ህጋዊ ሰውነቱ ተጠናክሮ በአሁኑ ሰዓት ከ12 ሽህ በላይ ተፋሰሶች ወደ ተጠቃሚነት



በተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ የህብረተሰቡ ተሳትፎ

ደረጃ ተሸጋግረዋል፡፡ በተጨማሪ ከአንድ ሽህ ዘጠኝ መቶ በላይ ደግሞ ስራ የተጀመረባቸውና በጥሩ አፈፃፀም ላይ የሚገኙ ተፋሰሶች አሉ፡፡ ሄደቱ ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻ የመጣበትን ሁኔታ ማረጋገጥ አስችሏል፡፡

ስለሆነም ተፈጥሮን የማልማት ፣ የመጠበቅና የመንከባከብ ስራው በአጭር ጊዜ የሚመጣ ሳይሆን በረጅም ጊዜ የሚመጣ መሆኑን ተረድተን እየሰራንበት ነው፡፡ ለእዚህ ደግሞ የአጭርና የረጅም ጊዜ ጥናቶች ተጠንተው እንደ ክልል ፲፲ ሚሊዩን ሄክታር የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ለመስራት እቅድ ተያዘ፡፡ በታቀደው መሰረት አሁን ላይ አንደ ክልል በተሰራው ስራ 8 ሚሊዩን ሄክታር የአፈርና የውሃ እቀባ ስራዎች መስራት ችለናል፡፡ እየታየ ያለው የሰብል ምርትና ምርታማነት ያደገው ተፈጥሮን ለመጠበቅ በተሰራው ስራ የመጣ ነው፡፡ አንዳንድ አካባቢዎች ከሰብል ምርት ወጥተው የነበሩ ለአብነትም እንደ አዊ ያሉ ዞኖች እና ሌሎችም አካባቢዎች የደን ልማት ውስጥ በስፋት ገብተው በርካታ ስራዎችን አሁንም ድረስ እየሰሩ ነው፡፡ እንደ አጠቃላይ በክልል ደረጃ ያለው የተፋሰስ ተጠቃሚነት ሲታይ በተሟላ መልኩ በሁሉም ነገር ላይ ለውጥ የታየበት ነው፡፡ በተሰራው ስራም የተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ጨምሮ በስራቸው በርካታ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ሰዎች አሉ፡፡ በዚህ በያዝነው ዓመት ለአንድ ሽህ አንድ መቶ አርባ ተፋሰሶች ህጋዊ ሰውነት ይሰጣል ተብሎ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡ እነዚህን ጨምሮ እንደክልል ወደ አምስት ሽህ የሚጠጋ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች የህብረት ስራ ማህበር ይኖራል ማለት ነው፡፡

በዚህ አመት በተደረገው የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራ ለማልማት የተሰጠው ከሶስት መቶ ስልሳ ስድስት ሽህ ሄክታር በላይ ይሰራል ተብሎ የታቀደ ነው፡፡ እቅዱ ከታቀደ በኋላ ሁሉም በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በአሁኑ ሰዓት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ጨምሮ ላለፉት ስድስት ወራት የትግበራ ስራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ታቅዶ እየተሰራ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ልማት በዘጠኝ ሽህ ሰማኒያ ሰባት ተፋሰሶች አካባቢ የልማት ስራው ይሰራል ተብሎ በተያዘው እቅድ መሰረት እየተሰራ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከተፈጥሮ ሀብት ልማት የትግበራ እቅድ ጎን ለጎን የአረንጓዴ አሻራ ልማት ስራው በታቀደው መሰረት የተፈጠሮ ሀብት ልማት ስራውን በሚያግዝ መልኩ ታቅዶ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና እንክብካቤ ስራ ለመስራት የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ግንዛቤ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ያለህብረተሰብ ተሳትፎ የሚለማ የተፈጥሮ ሀበት የለም፡፡ ስለሆነም እንደክልል በያዝነው ዓመት የተፈጥሮ ሀብት ልማታችንን ለማከናወን ከአንድ መቶ ስድስት ሚሊዮን በላይ ሰው እንደ ሚያስፈልግ እቅዱ ያመለክታል፡፡ ይህንንም የሚያስፈለገንን የሰው ኃይል በግብርና ኤክስቴንሽን አደራጅተን ወደ ስራ ገብተናል፡፡ እስካሁን ባለው ሂደትም አራት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የክልሉን ህዝብ በተፈጥሮ ሀብት ስራው ማሳተፍ ችለናል፡፡ ክልሉ ያለበት ወቅታዊ ሁኔታ ሳይገድበን የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ በተሰራው ስራ የነበረው የህዝብ ተሳትፎ ከጠበቅነው በላይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይሁን እንጅ በዚያው ልክ ችግሮችም አሉ፡፡ ስራው የዕለት ከዕለት ክትትልና የማህበረሰብ ተሳትፎ የሚያስፈለግወ ስለሆነ ያደራጀነው የሰው ኃይል ክልሉ ባጋጠመው ውቅታዊ ችግር ምክንያት በተከታታይ የመሳተፍ እና ተከታትሎ ለማሰራት አመች አለመሆኑ አንዱ በህብረተሰብ ተሳትፎ ላይ እያጋጠምን ያለ ችግር ነው፡፡ በእቅዳችን መሰረት ባሰማራነው የሰው ኃይል መጠን በተሰራ ስራ ሁለት መቶ ስድስት ሽህ ሄክታር በላይ መስራት ችለናል፡፡

የዘንድሮን የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራ ካለፉት ዓመታት ለየት የሚያደርገው አንዱ እንደ ክልል በችግርም ውስጥ ሆነን ስራዎች መስራት መቻላችን ነው፡፡ በያዝነው ዓመት ክልሉ በተለያዩ

# ልማት/ኢኮኖሚ



የለማ ተፋሰስ(ደቡብ ወሎ ወረኢሉ  ወረዳ)

ምክንያቶች ችግር ውስጥ እያለ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ስራዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ ለሁሉም አካባቢዎች እንደ ክልል አቅጣጫ መስጠት የሚቻልበት አይደለም፡፡ በመሆኑም በችግሩ ምክንያት ክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ስራውን ለማሰራት ከዞን ዞን ፣ ከወረዳ ወረዳ እና ከቀበሌ ቀበሌ የሚያወርደወ አቅጣጫ የተለያየ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለው ወቅታዊ ችግር የተነሳ እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጥናቶችን መሰረት አድርገን በመስራታችን ነው፡፡ ለእዚህ ደግሞ ችግሩን መሰረት ያደረገ የአሰራር ስልቶች መጠቀማችን የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ በሚገባው ልክ እንድንፈፅም አግዞናል፡፡ የተግባር ስራ አፈፃፀማችንን ስንገመግም ካለፉት አመታት የተሸለ መሆኑን በአፈፃፀማችን ላይ በታዩት ውጤቶች ማረጋገጥ ችለናል፡፡ በያዝነው ዓመት ተፈጥሮ ሀብትን በማልማት እንደክልል በተሰራው ስራ ተግባራትን በጥሩ ሁኔታ ስንፈፅም ህብረተሰቡን ሰብስበን ማወያየት በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን የታቀዱ ተግባራትን በጥሩ አፈፃፀም ማከናወናችን ለስራወ ምን ያክል ቁርጠኝነት በተላበሰ መልኩ መስራት እንደቻልን ያሳየ ነው፡፡

ለእዚህ ስራ መሳካት ዋናው ጉዳይ በዋናነት ከገጠመን ክልላዊ ችግር አንፃር ስራውን በኃላፊነት የሚይዝ ሰው መለየት ላይ ነበር፡፡ አመራሩ ምን ላይ ቢሰራ ይሻላል? ፣ የግብርና ባለሙያው ምንለይ መስራት አለበት እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ባለሙያው ምን ቢሰራ ይሻላል በሚለው ጉዳይ በጥልቀት ውይይት ተደረጎበት እንደ ክልል አንድ አቅጣጫ መቀመጡ ውጤታማ አድርጎናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተሰሚነት ያላቸውን ግለሰቦች ያሳተፈ ስራ መስራት መቻላችን ስራውን ይበልጥ በታቀደው ልክ ለማከናወን ችለናል፡፡ ስራው የበለጠ ተደራሽ እንዲሆን በአካል በመገኘት የመደገፍና የመከታተል ስራ ስንሰራ እኛ መድረስ በማንችልባቸወና ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ተጠቅመን ተደራሽ የማድረግ ስራ መስራት ችለናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እንደ ክልል እየተሰራ ባለው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ የአሁኑን የተፋሰስ ልማት ከሌሎቹ አመታት ለየት የሚያደርገው ጉዳይ ቢኖር ሁሉም የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራዎች እየተሰሩ ያሉት ግድብ ባለባቸው አካባቢዎች ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲሰሩ መደረጉ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተደረገው ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲሰሩ የተፋሰስ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ እቅድ አቅደን ለእዚህ ደግሞ  ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ህብረሰቡን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ልማዶች ላይ በስፋት መስራት በመቻላችን ነው፡፡ እንዲሁም እነዚህ በክልሉ እየተሰሩ ያሉት የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራዎች የቦታዎች ትክክለኛ መገኛ/Geo Located/ ውስጥ ተካተው መሰራታቸው ካለፉት ዓመታት የዘንድሮን ለየት የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ ነው፡፡

እንደ ክልል ያለፉትን ዓመታት ጨምሮ እስካሁን በተሰራው የተፋሰስ ሀብት ልማት ስራ ጉድለቶች ተስተውለዋል፡፡ እንደ ጉድለት እየተስተዋለ የመጣው እና ለተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ ስራው ላይ ባለቤት ሰጥቶ የመንከባከቡ ጉዳይ እስካሁን ያልተሻገርነው ችግር ነው፡፡ ተፋሰሱ ተለይቶ የተፋሰስ ኮሚቴ ከተመረጠ በኋላ የተሰራውን ስራ በትክክል የመቆጣጠር እና የመከታተል ችግር በስፋት ይታያል፡፡ በእዚህ ላይ የኮሚቴውን ኃላፊነት ወስዶ የኮሚቴውን ውሳኔ የሚደግፍ የህግ አካል እና የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ችግሩ እንዳለ እንዲቀጥል ያስቻለ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ወቅቱ በተቀያየረ ቁጥር የተፋሰስ ተቋማት የመጥፋትና የመዳከም አዝማሚያ ውስጥ መግባታቸው በተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ ጥበቃና እንክብካቤ ስራው ላይ ትልቅ ተግዳሮት ነበር፡፡ ለአብነትም በ1997 ዓ.ም እና በ2008 ዓ.ም ተፈጥሮ በነበረው ሀገራዊ ሁኔታ የክልላችን የተፈጥሮ ሀብት የችግሩ ገፈት ቀማሽ ነበር፡፡ በውቅቱ በተለያዩ የክልላችን አካባቢዎች የለሙ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች ጉዳት አስተናግደዋል፡፡ ሌላውና እስካሁንም ድረስ በተወሰነ መልኩ ያልተሸገርነው የህብረተሰቡ የግንዛቤ ማነስ ችግር በተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ ጥበቃና እንክብካቤ ስራው አሁንም ድረስ የሚሰተዋሉ እና መሻገር ያልቻልናቸው ችግሮቻችን ናቸው፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራውን በባለቤትነት ለመስራት ሁሉም አካል ስራው የእኔ ነው ብሎ በባለቤትነት ስሜት ለማከናውን መነሳት አለበት፡፡ ተግባሩ ለአንድ ዘርፍ ብቻ ተለይቶ የሚተው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሮ መኖሪያችን እና የሁላችንም የህልውናችን መገለጫ በመሆኑ ነው፡፡ ተፈጥሮ የሁላችንም የኑሯችን መጠቀሚያ በመሆኑ የምንሰራው ለማንም አይደለም ለምንኖርበት ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው የሚኖርበት መስራት አለበት ብለን እናምናለን፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሮን በርብርብ ማልማት ካልቻልን የምግብ ዋስትናን በሚባለወ ልክ በቀላሉ ማረጋገጥ አንችልም፡፡ ስለዚህ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የግድ ተፈጥሮ ሀብት ስራው ላይ ስር ነቀል ለውጥ ስራ መሰራት አለበት፡፡

ስርነቀል ለውጥ ለማምጣት ደግሞ ስራውን ለአንድ አካል ብቻ መስጠት የለበትም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ልማቱ ከፍተኛ የሆነ በጀት የሚያስፈልገው ስለሆነ ስራው በሚገባው ልክ በበጀት የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ መንግስት በዚህ ልክ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ ሲኖርበት እንደ ግለሰብ ማንኛውም ህብረተሰብ የራሱን አስተዋፅኦ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ በተለይም ደግሞ ተማርን የምንል ሰዎች ባለን አመለካከት ፣ ችሎታ እና እውቀት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤ በመፍጠር ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ተፈጥሮን በማልማት በመጠበቅና በመንከባከቡ ረገድ ግንበር ቀደም ሆነን መገኘት ይጠበቅብናል፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ከላይ እስከታች ድረስ ተደራሽነት ያለው የሚዲያው አካል የአንበሳውን ድርሻ ወስዶ ተፈጥሮን ሊታደግ ይገባል፡፡ ሁላችንም ባቅማችን ለክልሉ እጅና ጓንት ሆነን ተቀራርበን ከሰራን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንችላልን በማለት ሀሳብ አስተያየታቸውን አጠቀለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም አቶ እስመለዓለም ምህረቱ ለሰጡን ማብራሪያ እና ምላሽ እያመሰገነ የተቀናጀ እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ ስራ ምርታማነት በእጅጉ እንደሚጨምር ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ነገር ግን ሁሉም ነገር ጠፍቶ እጀን በእጀ የሚባለው ሳይደርስ ከወዲሁ ተፈጥሮን በማስቀጠል ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያመች የማድረግ ስራዎችን አጠናክሮ መስራት ይዋል ይደር የማይባል ተግባር ተደርጎ መሰራት እንዳለበት ያምናል፡፡

በመሆኑም ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን መንከባከብ እና የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠበቅ የተፈጥሮ አደጋዎችን መቋቋም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት የዚህ ትውልድ ኃላፊነቶች መሆናቸው ታሳቢ ያደረገ ትውልድ ተሸጋሪ ስራዎችን ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ የተፈጥሮ ሀብት ስራው ይበልጥ የተሳካ እንዲሆን በእቅድ በተቀመጡ የአሰራር ስልቶችና አቅጣጫዎች ላይ ከልብ መግባባት ላይ መደረስ አለበት፡፡

ተፈጥሮን በማልማት ፣ በመጠበቅ እና በመከባከብ በኩል ለህብረተሰቡ ሰፊ የግነዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራት ህብረተሰቡ ወደ ልማት ሙሉ በሙሉ እንዲገባ የሚያስችል በተግባር የተደገፈ ስራ መስራት ፣ የተፈጥሮ ሀብት ስራው በሰፊው ህዝብ በሚደገፍ ተሳትፎ እና ለዘርፉ መንግስት በሚያደርገው ትኩረት ስራውን ዳር ማድረስ የሚሉትን እና ከምንም በላይ የማህበረሰብ ተፋሰሶችን ወደ ተጠቃሚዎች ህብረት ስራ ማህበር የማሸጋገር ስራውን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል፡፡

ውሃማ አካላትና ተራራማ አካባቢዎች የትኩረት ማዕከል ማድረግ፣ አዲሱን የኤክስቴንሽን አደረጃጀትና የተፋሰስ ልማትን መሰረት በማድረግ መፈፀም ፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን ተግቶ በመስራት የአካባቢን ሥነ ምህዳር ከመለወጥ ባለፈ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ፣ በክልሉ የተፈጥሮ ፀጋዎችን በማልማትና የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ ማድረግ ፣ በየደረጃው የተፋሰስ ተጠቃሚነትን የማሳደጉ ተግባር ቀዳሚ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ዘላቂ ልማት መስራት የትውልድን ተጠቃሚነት ስለሚያረጋግጥ ሁሌም በየዓመቱ የሚሰራው የተፈጥሮ ሀበት ልማት ፣ ትበቃና እንክብካቤ ስራ መሬት የነካ እንዲሆን አስችሎ መተግበር አለበት፡፡

የተጀመረውን የአረንገዴ አሻራ ትግበራን ከአርሶ - አደር መር የተፈጥሮ ሃብት መልሶ ማገገም (FMNR) ስልቶች ጋር አቀናጅቶ በመስራት አላቂ የሆነውን የተፈጥሮ ሃብት ዘላቂ ለሆነው ለሰው ልጅ ፍላጎትን ለማስቀጠል ባለመ መልኩ የተፈጥሮ የቀድሞ ይዞታ እንዲመለስ ያስቻለ ዘመን ተሸጋሪ ስራ ከአሁኑ ትውልድ በእጅጉ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

በእዚህ ደረጃ የግብርና ምርታማነትን አሳድገን በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረገው ጥረት “ከማሳ እስከ ጉርሻ” ያለው የምግብ ዋስትና የተረጋገጠ እንዲሆን የሚያስችል ስራ ዘላቂ በሆነ መልኩ ተጠቃሚነቱ እየተረጋገጠ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ ተዘርግቶ ሁላችንም በተሰማራንበት የስራ መስክ የድርሻ የድርሻችን እንወጣ ተፈጥሮን እንታደግ እንላለን ሰላም፡፡

# የማይሻር ብሔራዊ ክብር

በፍሬው ምናለ

ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ራሱ ጥያቄው የኢትዮጵያን ያህል አንጋፋ ነው፡፡ ሲጀመር ኢትዮጵያ የሕይወታችን አካል እንጅ ጥያቄ የምናነሳበትና የምንመራመርበት ርእሰ - ጉዳይ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያዊነት በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ መሆን ነው፤ የአንዲት ኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ማንነት ነው፤ በኢትዮጵያ ማንነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ብሔርተኝነት ነው፤ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቅርፅ፣ ይዘትና አቅጣጫ የሚነድፍና የሚመራ ፍልስፍና ነው፡፡

ኢትዮጵያዊነት ማለት አንድነት ነው። የተለያዩ ጎሳዎችን አሰባስቦ መገለጫው ብሔራዊ የሆነ በመካከል አንድ ሀገራዊ ስሜትን የሚቀርጽ ኃይል ነው፡፡በጋራ በኢትዮጵያዊነታችን ድል ያደረግነው፣ የእገሌ ነው የማይባል፣ የሁላችንም ብሔራዊ ገድል ነው።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊነት በአንድ የተወሰነ ሀገር ውስጥ የጋራ አብሮነትን የሚያሳይ ዜግነት ነው፡፡ አንድ ጆሴ ኦርቴጋ የሚባል ፖርቹጋላዊ ጸሐፊ ሀገር የሚመሠረተው በምን ላይ ነው? ሲል ይጠይቃል፡፡ ሀገር የሚመሰረተው በእሱ አተያይ፣ በጋራ አብሮነት (common feature) ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነትም የጋራ አብሮነት ውጤት ነው፡፡ የጋራ መሠረት፣ የጋራ ጉዳይ፣ የጋራ እድል ያለውንና ወደፊትም የሚኖረውን መሠረተ - ሀሳብ የሚያስተናግድ ታላቅ መዋቅራዊ አውድ ነው፡ ለኢትዮጵያዊነት አንድነታችን መገለጫና ለማይሻር ብሔራዊ ክብር በሞዴልነት የአድዋ እና የማይጨውን ድል ማንሳት እንችላለን።

**ኢትዮጵያዊነት** የሕዝቧን አንድነት፣የመንግሥቷን ቀጣይነት፣ የግዛቷን ሉዓላዊነት፣የዜጐቿን እኩልነት የሚያነቃንቅ የአብሮነት አስተሳሰብ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት በርዕዮታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ አንድነት ላይ የቆመ ብሔርተኝነት ነው፡፡ በአጭሩ ኢትዮጵያዊነት የአንድ ሀገራዊ ብሔር (ኅብረ-ብሔር) ማንነትና ፍልስፍና ነው፡፡ ዘመን የማይሽረው የኢትዮጵያዊነት ህልውና አዕማድ (ምሰሶዎች) ሕዝብ፣ ሀገርና መንግሥት ናቸው፡፡ ሥርወ ቃሉ ግእዝ የሆነው "ብሔር" የእነዚህ ሦስት አካላት ድምር ውጤት ነው፡፡

**ሕዝብ - ኢትዮጵያ፦** የኢትዮጰያዊነት መገኛ ግዙፍ አካል ነው፤ ሕዝብ የሌለው ማንነትና ብሔርተኝነት ሊኖር አይችልም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ብሔራዊ አቋም ያለው፣ ማሕበረሰብ የሚያስፈልጉትን ዐበይት መሥፈርቶች የሚያሟላ፣ የጋራ ስም፣ የጋራ ሀገር፣ የጋራ መንግሥት፣ የጋራ ታሪክ፣ የጋራ ህግና ባህል ያለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ በጋራ ተስፋ የተሳሰረ ቤተሰብ እንጅ በልዩነት የተዳበሉ ሕዝቦች ጥርቅም አይደለም፡፡

**ሀገረ ኢትዮጵያ፦** በድርቡ ግዛታዊና መልክዐ - ምድራዊ ቁመናን፣የታሪክና የባህል ማህደርነት፣ እንዲሁም የወላጅነትንና ፈጣሪነትን ባህሪ አስተሣሰብ ትይዛለች፡፡ ሀገረ ኢትዮጵያ ከሕዝብና ከመንግሥት የሚዋረስ ስብእና ያላት ምድር ናት፡፡

***መንግሥተ ኢትዮጵያ፦*** በዋነኛነት አስተዳደራዊ ተቋሙን፣ አልፎም ወጉን፣ሥርዓቱን፣ህጉንና ታሪኩን የሚገልፅ ግንዛቤ ነው፡፡ ልዕለ - ዘውጋዊ ተቋምና የብሔራዊ አንድነቷ ማሠሪያ የሆነው መንግሥት የኢትዮጵያዊነት ጠንሳሽ፣ የህልውናዋ ዘብ፣ የስልጣኔዋ፣ የክብርና ኩራቷ መለዮ ነው፡፡

በመግቢያነት የገለጽነውን ሀሳብ ያቀረብነው ሐዲስ መጽሄት በባህልና ታሪክ አምድ በመጋቢት 2017 ዓመተ ምሕረት እትሙ ላይ ህልውናው በሕዝብ፣ ሀገርና መንግሥት ላይ ስለሚያጠነጥነው ኢትዮጵያዊነት መረጃ መስጠት ስለፈለግን ነው፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አምናና ዘንድሮ በሚል ርእሰ - ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጡን የታሪክ ጥናትና ምርምር ባለሙያ አነጋግረን ሙሉ ሀሳቡን ይዘን ቀርበናል፡፡ ተከታተሉን መልካም ንባብ፡፡

ያቀረብንላቸውን ጥያቄዎች መሠረት አድርገው ተከታዩን ምላሽ የሰጡን አቶ ዳምጤ ደምሴ ይባላሉ፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህል ቱሪዝም ቢሮ የታሪክ ጥናትና ምርምር ባለሙያ ናቸው፡፡

***ሐዲስ፦*** ኢትዮጵያዊነት ማለት ምን ማለት ነው?

**አቶ ዳምጤ፦** ኢትዮጵያዊነት ማለት የኢትዮጵያ ህዝብ በጋራ የገነባቸው አገራዊ መገለጫዎችን የሚወክል ነው፡፡ኢትዮጵያዊ ማንነት ሲገነባ ብዙ እና የተለያዩ ንዑሳን ማንነቶችን በማጣመር ለዘመናት በማብላላትና በማያወላዳ መልኩ ለባለቤቱም ሆነ ለተመልካቹ የታወቀና የፀና መገለጫ ነው፡፡ ለምሳሌ ከጥንት ታሪክ እንደምንረዳው ኢትዮጵያዊያንን በአካል አግኝተው የተረዱ እና ስለእነሱ መረጃ ያገኙ ኢትዮጵያዊያንን እንዲህ ናቸው ብለው ምስክርነት አስቀምጠዋል፡፡

የጥንት የግሪክ ተጓዥ አሳሾች እና ታሪክ ጸሐፊዎች ለምሳሌ ፕሊኒ፣ ሔሮደተስ ሆሜር፣ ኮስማስና የመሳሰሉት ኢትዮጵያዊያን ስለሚባሉ ህዝቦች መገለጫ ያሉትን የጋራ ማንነት አስቀምጠዋል፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት በተለይ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቁራን ኢትዮጵያዊ ማንነት ተገልጧል፡፡

በመካከለኛው ዘመንም እነአልቫሬዝ በኋላም የተለያዩ የአውሮፓ አሳሾች ፣ አጥኚዎችና ሰላዮች ስለ ኢትዮጵያዊያን እና ኢትዮጵያዊነት በየማስተዋዋቻቸው ጽፈዋል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊነት ሲባል በተለያዩ ዘመናት ከውስጥና ከውጭ የሚደረጉ የህዝቦችን ግንኙነት መሠረት አድርጎ የሚገነባና ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይ መታወቂያ፣መገለጫ እና የጋራ ጠባይ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያዊ ማንነት ፍፁም የማይዘባና ቋሚ ላይሆን ይችላል፡፡ ማንነት የህዝቦች የጋራ እንቅስቃሴ ውጤቶች እንደመሆኑ መጠን በጊዜ ሂደት ሊበረዝ፣ ሊከለስ ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡ይህ ለውጥም

# ባህል/ታሪክ



አቶ ዳምጤ ደምሴ

በአማራ ባህል ቱሪዝም ቢሮ የታሪክ ጥናትና ምርምር ባለሙያ

በከፊል ወይም በሙሉ ሊሆን ይችላል፡፡ ባህል፣ ቋንቋ፣ አኗኗር፣ አስተሳሰብ ሲለወጥ ማንነትም በዚያው ልክ የቅርፅ ወይም የይዘት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፡፡

ኢትዮጵያዊ ማንነትም በዚህ ሂደት ያለፈ ነው፡፡ ከሞላ ጎደል ለረዥም ጊዜ የሚታወቀው ኢትዮጵያዊነት ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፣ በህግ የሚያምን፣ ለሀገሩ ነፃነት ዘብ የሚቆም፣እንግዳ ተቀባይ ወዘተ በሚሉ እሳቤዎች የሚገለጥ ነው፡፡

**ሐዲስ፡-** ቅድመ ኢህአዴግ የነበረው ትውልድ ከኢትዮጵያዊነት አኳያ ታሪካዊ ፋይዳውን ለአብነት ጠቅሰው ቢያብራሩልኝ?

**አቶ ዳምጤ፡-** ቅድመ ኢህአዴግ የነበረው ትውልድ እንደተባለው ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት፣ አንድነትና እድገት የሥራ በኢትዮጵያዊ ማንነቱ የሚኮራ እንደነበር ማንሳት ይቻላል፡፡

በእኔ እምነት እስከ 1983 ዓመተ ምሕረት ድረስ የነበረው የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ ከሞላ ጎደል ወጥና ቀጣይነት ያለው ነበር፡፡ በዚያን ዘመን የነበረው ኢትዮጵያዊነት የአገር ፍቅርን፣ ሞራላዊነትን፣ ፈሪሃ - እግዚአብሔርን፣ ህግ - አክባሪነትን፣ ጨዋነትን እና አልበገር - ባይነትን አይተንበት አልፈናል፡፡

ለሀገር ግንባታ መሠረቶች ደግሞ ሀገርን መውደድ፣ ህግን ማክበር፣ ለህግና ስርዓት ተገዥ መሆን፣ ለሀገርና ለራስ መቆም፣ ስራ ወዳድና ታታሪነት ወሳኝ ነገሮች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ዜጎች ሀገሬ ብለው በገነቡት ሀገር፣ ለነፃናትና ለክብር ብለው መስዋዕትነት በከፈሉበት ሀገር፣ በነፃነት ተንቀሳቅሰው በመረጡትና ለኑሮ ይመቸኛል ባሉት አካባቢ ቤት መሥርተውና ሀብት አፍርተው መኖር የቻሉበት ዘመን በዋናነት ቅድመ ኢህአዴግ የነበረው የታሪክ ዘመን ነው፡፡

ለአብነት ኢትዮጵያዊነት በዘመናት በህዝቦች የጋራ መስዋዕትነት በጽናት የተገነባ ስለመሆኑ ኢትዮጵያ ከውስጥና ከውጭ የተነሱባትን ጠላቶች በጋራ በመከላከል የጻፉትን ደማቅ ታሪክ ማየት ይቻላል፡፡ በ16ኛዉ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ቱርኮች አህመድ ግራኝን በጦር መሳሪያና በወታደራዊ የሰዉ ኃይል በማገዝ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ባደረጉት ጥረት ኢትዮጵያዊያን ለ15 ዓመታት ባደረጉት ተጋድሎ በአሸናፊነት ተወጥተዋል፡፡

ግብጾችም የአባይ መነሻ የሆነዉን ደጋማ የኢትዮጵያ አካባቢ ለመቆጣጠር በሚል ተደጋጋሚ ወረራዎችን በማድረግ በተለይ ጉራ እና ጉንደት ላይ በኢትዮጵያዊያን በደረሰባቸዉ ሽንፈት ኢትዮጵያን ለመውረር እንዳይሞክሩ ተደርጓል፡፡

ሶማሊያ ከቅኝ ግዛት ነጻ ከመውጣቷ ታላቋን ሶማሊያ እንገነባለን በሚል የኢትዮጵያን ግዛት በመውረር በርካታ ኪሎ ሜትሮችን መቆጣጠር ችላ ነበር፡፡

ይሁን እንጅ በዚህ ከፍተኛ ቁጣ የተሰማቸው ኢትዮጵያዊያን ባደረጉት የጋራ ርብርብ ድባቅ በመምታት አገራቸውን ነጻ አውጥተዋል፡፡ በአውሮፓዊያን የቅኝ ግዛት ቅርምት ዘመን ጣሊያን ኢትዮጵያን እንድትይዝ እጣ ወጣላት፡፡

ይህን ተከትሎ ጣሊያን ሰሜን ኢትዮጵያን ለመውረር ሞክራ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በአንድ ቃል ተናጋሪ በአንድ ልብ አሳቢ ሆነው ጠላትን በመምታታቸው ኢትዮጵያ አድዋ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ እንፀባራቂ ድል አስመዝግባለች፡፡ ኢትዮጵያዊያን ነጻነታቸዉን አስከብረዉ ለዘመናት የዘለቁት ለነጻነታቸው ባላቸዉ ቀናዒነት፣ ጽናትና አንድነት ነዉ፡፡ ኢትዮጵያዊያን ቀዬ እና ጎሳ ሳይመርጡ ለሀገራቸዉ የከፈሉት መስዋእትነት፣ በመረጡት የአገራቸዉ አካባቢ እየተዘዋወሩ ሰርተው መኖር ይችሉ የነበረው ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት ስሜት፣ ክብር እና ኩራት ስለነበራቸው ነው፡፡ ይህ ሁሉ የድል ውጤት

የተመዘገበው በምንም ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ኃይል ነው፡፡

**ሐዲስ፡-** በኢትዮጵያዊነትና ሀገር ግንባታ ዙሪያ የአሁኑን ትውልድ እንዴት ይገልጹታል?

**አቶ ዳምጤ፡-** የአሁኑ ኢትዮጵያዊነት የተደበላለቀና እንዲህ ነው ብሎ ብያኔ ለመስጠት የሚያስቸግር ነው፡፡ በዘመነ ኢሕአዴግ ከ1983 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ባለው ትውልድ ኢትዮጵያዊ ማንነቶች ርዕዮተ ዐለማዊና መዋቅራዊ በሆነ መንገድ እየተሸረሸሩ በመምጣት ነባሩን የኢትዮጵያዊ መገለጫ እንዲዛባ አድርገውታል፡፡

በዚህ ዘመን ኢትዮጵያዊነት አይበረታታም፤ ይነቀፋል፤ ይኮነናል፡፡ ህዝቦች ኢትዮጵያዊነትን እንዲገነቡ ስላልተሰራ አለፍ ሲልም ከደረሰባቸው የተከማቸ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግር ምክንያት እንዲንቁት፣ እንዲያፍሩበትና እንዲሸማቀቁበት ተደርጓል፡፡

ከትልቁ ኢትዮጵያዊነት የጋራ ማንነት ይልቅ የተሰራበት፣ የተበረታታውና የሚያኮራ የሚመስለው ንዑስ የጎሳ ማንነት ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያዊነት እየላላና እየደበዘዘ የመጣው እየተፈራረቁ ወደ ስልጣን የመጡ ኃይሎች የብሄርተኝነት አቀንቃኝ በመሆናቸው ለኢትዮጵያዊ ማንነትና አንድነት ትኩረት ስለማይሰጡት ነው፡፡ አሁን አሁን ኢትዮጵያዊነት የአማራ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ አማራ ደግሞ በእነርሱ ዓይን ጨቋኝ፣ አሀዳዊ፣ጨፍላቂ አድርገው የሚመለከቱት ስለሆነ የሚበረታታና የሚወደድ እሴት አይደለም፡፡

ስለዚህ ባለፈው ማለትም በቅድመ ኢህአዴግ በነበረውና አሁን ባለው ኢትዮጵያዊነት መካከል ከፍተኛ ተቃርኖ ይታያል፡፡ በሁለቱ የአፍራሽና የገንቢ፣የጨለማና የብርሃን፣የአንድነትና የመለያየት ተቃርኖ ጎልቶ ይታይባቸዋል ፡፡ አንድ ነገር ጠቃሚ ነው ወይስ አይደለም? በጎ ነው ወይስ መጥፎ? ብሎ ለመፈረጅ ውጤቱን አይቶ መበየን ተገቢ ነው፡፡

ስለዚህ ዛሬ ኢትዮጵያዊነት የሚባል መገለጫ አለ ብየ አላምንም፡፡

ምክንያቱም በጋራ ሁሉም ተስማምቶ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ ኢትዮጵያዊነት ማለት ደግሞ እንዲህ ነው፤ በማለት አፍን ሞልቶ ለመናገር አስቸጋሪ ደረጃ ላይ ስለደረሰ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ቀድሞ ኢትዮጵያዊነት ነበር፤ ዛሬ ደግሞ የለም፡፡ ይህ የሚያሳየው የነበረን ነገር ከሌለ ነገር ጋር ማወዳደር የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ መሆን ያለበት ምን አልባት ኢትዮጵያዊነትን ወደፊት ጠግነንና ገንብተን ትክክለኛ መገለጫ ያለው ብያኔ ልንሰጠው እንችል ይሆናል፡፡

**ሐዲስ፡-** ከንጽጽሩ ማብራሪያ በመነሳት የተሻለ ነው ያልነው ትውልድ የተሻለ እንዲሆን ያደረጉት መሠረታዊ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

**አቶ ዳምጤ፡-** በነበረው ሥርዓት ሁሉም ዜጋ በዋናነት አንዲት ኢትዮጵያ ብሎ የሚያምን እንጅ በቋንቋ፣በብሔር፣ በዘር፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉት ልዩነት በመፍጠር የተበታተነ ስላልነበር ነው፡፡

በዚሁ በነበረው ጽኑዕ ኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪ እየተከላከለ ነፃነቷን አስጠብቃ ለሰፊ ዘመናት እንድትኖር አድርጓታል፡፡

**ሐዲስ፡-** አሁን ላይ ያለው ትውልድ ከኢትዮጵያዊነት አንጻር በተሻለና በታነፀ ሥነ - ምግባር ተቃኝቶ ለሀገር ግንባታ ተባባሪ እንዲሆን ምን ምን ተግባራት መሠራት አለባቸው? ከማንስ ምን ይጠበቃል ይላሉ?

**አቶ ዳምጤ፡-** የቅርጽም ሆነ የይዘት ችግር ያለበትን ኢትዮጵያዊነት ለብያኔ አስቸጋሪ የሆነ እሳቤ ልተወውና እንደ ሀገር የሚበጀንን ነገር ላንሳ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ህዝቦች በጋራ ለመኖርና የጋራ ማንነትን ለመገንባት በራሳቸው ፈቃደኝነት ስምምነትን መምረጥ አለባቸው፡፡ በእኩልንት፣ በጋራና በአንድነት ለመኖር ሲወስኑ የጋራ ማንነትን መገንባት ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ንዑስ ማንነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ አገራዊ የጋራ ማንነቶችን መገንባት ይቻላል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የጋራ አገራዊ ህልም ሲኖር ነው፡፡

ስኬታማ የሚሆነው በርዕዮተ- ዓለማዊ ፣ በመዋቅርና በህዝቦች ቀና ፍላጎት ሲታገዝ እንጅ ወደ ተግባር የሚቀይር የጋራ ዓላማ፣ ግብ፣ ርዕዮትና መዋቅር ሳይኖር ሊመጣ የሚችል የሀገር ግንባታ የለም፡፡ ይልቁንም መለያየት፣ መጋጨት፣ የሰላም ዕጦት፣ ኋላቀርነት ገሀድ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የአንድ ሀገር ህዝብ የኔ ሳይሆን የኛ የሚለው የጋራ መገለጫ ሊኖረው ይገባል፡፡ ጥረቱ ሁሉ ሀገራዊ ፍላጎቱንና ህልሙን እውን የሚያደርግ ልማት መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ በነፃነት መነጋገር፣መወያየት፣ ሕዝብና መንግሥት የጠነከረ ግንኙነት ማድረግ፣ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድ በጋራ ማዘጋጀትና ሁሉም የሚበጀውን መውሰድ ይጠቅማል፡፡

ኢትዮጵያዊነት ዳግም እንዲያብብና ፍሬያማ እንዲሆን ልሂቃኑ ለእውነት በመቆም መንግሥት ሲሳሳት መገሰጽ፣ ማረምና ሚዛን እንዳይስት ለማድረግ መሥራት አለባቸው፤ምሁራን ከአድርባይነት፣ ከጥቅመኝነትና ከምንአገባኝነት አስተሳሰብ ወጥተው ለሙያቸው፣ ለህዝባቸው እና ላለባቸው የትውልድ ኃላፊነት በታሪክ ተወቃሽ እንዳይሆኑ ድርሻቸውን ባግባቡ ሊወጡ ይገባል፡፡

ወጣቱ በበኩሉ የዛሬና የነገ የሀገር ባለቤትና ባለአደራ መሆኑን ተረድቶ ኢትዮጵያ ለነገ በምትሰራው ዛሬ በንቃት፣ በኃላፊነት እና በቁርጠኝነት መሥራት አለበት፤ ቴክኖሎጅው የላቀ ደረጃ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት ከዘመኑ የዐለም ሁኔታ ጋር ለመወዳደር የሚያስችል እውቀትንና ክህሎትን ሰፋ ባለ አመለካከት በመመራመርና የተሻለ በመፍጠር፣ ሁለንተናዊ ነጻነትን ማስከበር አለበት፡፡

አባቶቹ በመስዋዕትነት ነፃነቷን አስከብረው ያስረከቧትን ሀገር ወጣቱም ይህን አደራ ለማስቀጠል እና ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ በርትቶ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

# ባህል/ታሪክ



ለኢትዮጵያ አንድነትና ዘመናዊነት ዋጋ የከፈሉ ታላቅ አባት

ሁሉም በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በፍትሐዊነት የሚኖርበት የጋራ ሀገር ያስፈልጋል፡፡ ዜጎች በምርጫቸው፣ በፍላጎታቸውና በችሎታቸው የህግ ጥበቃ ተሰጥቷቸው ሀገሬ በሚሉት የትኛውም አካባቢ መኖር መቻል አለባቸው፡፡

ይህን ነገር ለመፍጠር በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ ወሳኝ ቢሆንም ስልጣንንና መዋቅርን የተቆጣጠረው መንግሥት ደግሞ የአንበሳውን ድርሻ ሊወስድ ይገባል፡፡

ይህን ሥንሰራ የእኔነትን እሳቤ ሳይሆን የእኛነትን አመለካከት አዳብሮ ከእያንዳዱ ግለሰብ ጀምሮ ሲቪክ ማኅበራት፣የእምነት፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሚናቸው ሀገርን ማሳደግ ላይ ሊሆን ይገባል፡፡ በማለት ሀሳባቸውን አጠቃለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም ከታሪክ እንደሚረዳው ኢትዮጵያ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጠላቶቿ ራሷን ተከላክላና ነፃነቷን አስከብራ ለመኖር ኢትዮጵያዊነት መተኪያ የሌለው ሀብቷ እንደሆነ ያምናል፡፡

ኢትዮጵያዊነት ባህላዊ ዕሴታችን፣ እምነታችን፣ አብሮነታችን፣ ማኅበራዊ ግንኙነታችን፣ ቅርሳችን፣ ነጻነታችን፣ ብሄራዊ ክብራችን ወዘተ ሊገለጽ የሚችልና በተለይ ለአንድነት ትልቅ መሰረት ነው፡፡

በዓለም ታሪክ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የራሷ ፊደል፣ቋንቋና ባህላዊ መገለጫ ያላት ናት፤ በአፍሪካ ሀገራት ለቅኝ ግዛት ያልተንበረከከች፣ የጥቁሮች የነፃነት ተምሳሌትና ቴክኖሎጅ ባልነበረበት ጥንት ዘመን ጣሊያንን ያክል ሀገር አሸንፋ የድል ባለቤት የሆነችና በዓለም አቀፍ ደረጃ አንቱ የተባለች ብቸኛ የምሥራቅ አፍሪካ አብሪ ኮከብ መሆኗን ታሪክ የሚመሠክረው ሀቅ ነው፡፡ እነአቡነ ጴጥሮስና አፄ ቴዎድሮስ የተሰውላትንና የአባቶች አጥንትና ደም አለት ሆኖ ያጸናትን ኢትዮጵያ ጠላት አይደለም ሊያፈርሳት ንቅንቅ ሊያደርጋት አይችልም፡፡

በዓለም የሌሉ የብርቅየ ዱር አራዊት፣ የተለያዩ ቅርሶች፣የታላላቅ ተራራዎችና የኤሌክትሪክ ማመንጫ ወንዞቻችን ሁሉ ባለቤት በሆነች ኢትዮጵያ ላይ ኢትዮጵያዊነት የለም ማለት ማንነቷ እየተሸረሸረ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የማትቀጥልበት ደረጃ ላይ ደረሰች ማለት ነው፡፡

ይህን ችግር ቆመን የምናየው ስላልሆነ "ሳይቃጠል በቅጠል" እንዲሉ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከመንግሥት፣ ከምሁራንና ከወጣቱ በተጨማሪ የሃይማኖት አባቶችና እድሜ ጠገብ ታሪክ አዋቂዎች ለልጆቻቸው ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡ የአሁኑ ትውልድ ስለኢትዮጵያ እናትነትና ምንነት በሥርዓተ - ትምህርት ተቀርጾ ከታች እስከ ከፍተኛ የትምህርት እርከን ድረስ የመማር ማስተማሩ ሂደት በስፋትና በጥራት እየተከናወነ ዜጋው ግንዛቤ ኖሮት ለሀገሩ ተቆርቋሪና ነፃነቷን አስከባሪ እንዲሆን መስራት ይገባል፡፡

በተጨማሪም ሁሉም ዜጋ የራሱን ቋንቋ፣ ነገድ፣ ባህል፣እምነት፣ወዘተ በነፃነት አስጠብቆ ከመኖር ባለፈ የእኛ የሚለውን ኢትዮጵያዊነት በተቆርቋሪነትና በባለቤትነት ማሳደግ ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የሁሉም እናት ስለመሆኗ ለአፍታም መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነውና፡፡

በዚህ አግባብ መለያየትን ትቶና አንድነትን አበርትቶ መሥራት ከተቻለ ሀገሪቱን ማስቀጠል ብቻ ሳይሆን ወደተሻለ እድገት ማሻገር ይቻላል፡፡ በማለት የዛሬውን በዚህ አጠናቀቅን፡፡ ለሁሉም ሰላም ይቅደም!!

# ትውልድ የማዳን ርብርብ

በደፋሩ እምሬ

ፀሐፍት “አገር ማለት ሰው ነው” እንደሚሉት አገር “ሰው” እንድትሆን በሁለንተናዊ መልኩ አገሩን የሚያበለጽግ ታማኝና ለወገኑ ተቆርቋሪ ትውልድ ያስፈልጋታል፡፡ ከትውልድም በተለይ “ወጣት” የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል የላቀ ድርሻ አለው፡፡“ወጣት የነብር ጣት” እንደሚባለው በበጐ ገጽታው ሲዳሰስ ወጣቱ ከፍተኛ የስራ ፍቅር፣ እምቅ የፈጠራ ችሎታና እውቀት፣ ከፍተኛ የጉልበት ክምችት፣ ወዘተ. ባለቤት መሆኑ በተጠየቅ እሙን ነው፡፡

አገር ገንቢና ተረካቢ የሆኑት ወጣቶች ጤናቸው ተጠብቆ፣ በመልካም ስነ-ምግባር ታንፀው፣ በራሳቸው ተማምነው፣በእውቀት፣በክህሎት፣ በአመለካከትና በአካል ዳብረው ማደግ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ መልኩ ወጣቶችን ለማነፅ ትልቅ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ጥረት እያደረጉ ከሚገኙት የመንግስት ተቋማት መካከል “ወጣቶች” እና “ታዳጊዎች” የሚባሉትን የትውልድ ክፍሎች ዋና ትኩረት አድርጐ በፌዴራል ከሚኒስተር ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ጉዳዮቻቸውን የሚመራው “ወጣቶችና ስፖርት” ተቋም ይጠቀሳል፡፡

በኢትዮጵያ ብሄራዊ ወጣቶች ፖሊሲ መሰረት “ወጣት” የሚባሉት ከ15 እስከ 29 እድሜ ያላቸው ሲሆኑ “ታዳጊ” የሚባሉተ ደግሞ ከ15 እስከ 18 እድሜ ምድብ ያላቸው ናቸው፤ በማለት ገለፃቸውን የጀመሩት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የወጣቶች ስብዕና ልማት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ደሳለኝ ይታየው ናቸው፡፡

ተቋሙ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በተለየ ለምን ትኩረት አድርጐ መስራት አስፈለገው በሚል ላቀረብንላቸው ጥያቄም ምላሽ ሲሰጡ ዋናው ጉዳይ ብሔራዊ ወጣቶች ፖሊሲ ነው፡፡ ፖሊሲው የወጣቶች ችግሮች ናቸው ብሎ የለያቸው 10 የራሳቸው የሆኑ ቁልፍ የፖሊሲ ጉዳዮች ተብለው የተለዩ ችግሮች ለምሳሌ የመልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣የጤና ፣የአለም አቀፍ ግንኙነት፣ የትምህርትና ጥራትና ተደራሽነት ፣ የስፖርትና መዝናኛ ወዘተ. ለመፍታት ታላሚ የተደረገ ነው ብለዋል፡፡

የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እነዚህን ቁልፍ የወጣቶች ችግሮች ለመፍታት ብቻውን እና ሌሎች የመንግስት ተቋማትን በማስተባበር አብሮ ይሰራል፡፡ ብቻውን አቅዶ የሚሰራቸው በርካታ ተግባራት ያሉት ሲሆን ዋና ዋና ከሚባሉት መካከል የመጀመሪያው የወጣቶችን አጠቃላይ መሰረታዊ መረጃዎች በማደራጀትና በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡ ሁለተኛው ወጣቶች መንግስት ከሚያቀርባቸው አጠቃላይ ግብዓቶችና ልማቶች እንዲጠቀሙ በአመለካከት ይገነባል፡፡ ሶስተኛው በተበታተነ ሁኔታ የሚገኙ ወጣቶችን በተለያዩ አደረጃጀቶቸ በማስገባተ፣የመደራደር፣የመስራት፣የፈለጉትን የመሆንና የማሳካት አቅም ፈጥረው ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህራዊ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር በንቃት ተሳታፊ እንዲሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር ስራ እንደሚሰራ ገልጸውልናል፡፡

ቢሮው ከሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ጋር የሚሰራቸውን ስራዎች አስመልክቶ ሲያብራሩ ደግሞ “የወጣቶች ቁልፍ ችግሮች በተቋማቱ ውስጥ ዋና ጉዳይ ሆነው ተካተው እንዲሰሩ በዋናነት የመምራት፣የመቆጣጠርና የማስተባበር ስራን ይሰራል፡፡ “የወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ ምክር ቤት” የሚባለውን በማስተባበር የወጣቶች ዋና ችግር የሆነውን የኢኮኖሚ ክፍተት ለመፍታት የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው በየደረጃው በተቋቋመው የወጣቶች ምክር ቤት ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ሌላው አሁን ላይ ወጣቶቻችን ከፉኛ እያሳጣን ያለውና የዚህ ጹሁፍ የዳሰሳ ትኩረት የሆነው አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች የሚያደርሱትን ጉዳት ለመከላከል ከላይ እስከታች ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት የተመሰረተውን ግብረ ሃይል አደረጃጀት በዋናነት የመምራትና የማስተባበር ስራ እንደሚሰራ ተናግረዋል።

አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች ወጣቶችና ታዳጊዎች መልካም ስነ-ምግባር ተላብሰው እንዳያድጉና ከጤናማው የህይዎት መስመራቸው እንዲወጡ በዋና መሰናክልነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በወጣቶችና ታዳጊዎች ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ማብራራት የጀመሩት “አሉታዊ መጤ ልማድ” ምንድነው የሚለውን በመግለጽ ነው፡፡ “ልማድ” የሚባለው አንድ ድርጊት ሆን ተብሎ ወይም በአጋጣሚ ይሁን በተደጋጋሚ በአንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ሲከወን ወይም ሲነገር ነው፡፡ “አሉታዊ መጤ ልማድ” የሚባለው ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ ባህልና ልማድ ያልሆኑ፤ነገር ግን በተለያዩ ክዋኔዎች ከሌላ ተወርሰው ወደ ማህበረሰቡ የገቡና በማህበረሰቡ ባህልና ልማድ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጎጅ ነገሮች ናቸው(አዎንታዊ ልማዶችም እንዳሉ ልብ ይሏል)። ለአሉታዊ መጤ ልማዶች አብነት የሚሆኑት ልብስን ቀዳዶ መልበስ፤ወንዶች ፀጉርን አንጨብርሮ ማሳደግ፤ሀፍረተ ስጋን የሚያጋልጥ ራቁት የሴቶች አለባበስ፤ወንዶች ጉትቻ/ሎቴ/ ማድረግ፤ወንዶች ሱሪያቸውን ከወገብ አውርዶ መልበስ፤ የምሽት ራቁት ጭፈራ ቤቶች፤ቁማርተኝነት፤ግብረ ሰዶማዊነትና ግለኝነት አስተሳሰብ፣ወዘተ. የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ወጣቶችና ታዳጊዎች ለእነዚህ አሉታዊ መጤ ልማዶች ሰለባ በመሆን የራሳቸውን ባህልና ልማድ ሲረሱና ሲያበላሹ ይስተዋላል። ይህ ክስተት በሂደት የማንነቱን መገለጫ ያጣ ትወልድ ይፈጠርና አገር አደጋ ላይ ትወድቃለች ብለዋል።

አደንዛዥ እፆችን በሚመለከት በሰጡት ማብራሪያም እንደአሉታዊ መጤ ልማዶች ሁሉ በወጣቶች ላይ ሁለንተናዊ ጉዳት እያደረሱ የሚገኙ በእንክብል ፣ በፈሳሽ፣ በማሽተት ፣ በማኘክና በጭስ መልክ የሚጠቀሟቸው ናቸው። እንደክልል በተጠቃሚዎች ፣ በሱሰኞች ፣ በነጋዴዎች፣ በአቅራቢዎችና በአቅርቦት ብዛት የአደንዛዥ እፅ



"በጉዳቱ አሳሳቢነት ልክ ትኩረት ሰጥተን ካልተረባረብን ወጣቶችንና ታዳጊዎችን እያጣናቸው ነው"

አቶ ደሳለኝ ይታየው

እንቅስቃሴውን ጫት እንደሚመራውና አሁን አሁን ከአደንዛዥ እፅ ምድብነት ወጥቶ ከጓሮ አትክልቶች ጋር የተመደበ በሚመስል መልኩ ውሃ—ገብ የሆኑ በመስኖ መልማት የሚገባቸው አያሌ መሬቶች በጫት ተክል ተሸፍነዋል። ከእነዚህ መሬቶች የሚለቀመው ቀንበጥ ጫት በአደባባይ እየታሸገ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በእየለቱ ወደ አዲስ አበባ፣ጎንደር፣ደሴ፣ኮምቦልቻ ሲጓጓዝ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ጫት ትውልድን በተለይ አገር ተረካቢ የሆኑ ተተኪ ወጣቶችን የሚጎዳ አደገኛ አደንዛዥ እፅ መሆኑ ባልተፃፈ ህግ ተቀባይነት አግኝቶ "በአይኔን ግንባር ያድርገው" እሳቤ ትልቅ የገቢ ምንጭ ተደርጎ የደራ ገበያ ፈጥሯል፡፡ ጫትን መጠቀም የማይታወቅባቸውና እንደ ርኩሰት የሚታይባቸው የምዕራብ አማራ አካባቢዎች እንኳን አሁን ላይ በየመንገዱ፣በየሜዳው፣በየታከሲው የሚጠቀሙ አያሌ ወጣቶቶን መመልከት የተለመደ ሆኗል፡፡ እንዲህ አይነት ሀላፊነትና ተጠያቂነት የሌለበት የጫት አጠቃቀም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የክልሉን ወጣቶች ሱሰኛ አድርጎ የጫት መቃሚያ ገንዘብ ሲያጡ፣ ወደ ስርቆት፣ ሰው መግደል፣ ወንጀሎች እንዲሰማሩ እያደረጋቸው መሆኑን ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት ገልጸዋል።

አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች እያደረሱት ያለውን ጉዳት ለመከላከል መፍትሄዎች ምን ምን እንደሆኑ እንዲነግሩን ለአቶ ደሳለኝ ያቀረብንላቸው ሌላው ጥያቄ ነበር። ለዚህም ምላሽ ሲሰጡ "ጉዳዩ አንዳች አሻጋሪ የሆነ የማዳከምና የመከላከል አብዮት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ አብዮት በጥናትና ምርምር ላይ በተመሰረተ መረጃ መመራት ስላለበት አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች በክልል ደረጃ ያሉትን የአሳሳቢነት ደረጃ በሚመለከት ባህርዳር ዩኒቨርስቲና ሌሎች በክልሉ ያሉ ዩኒቨርስቲዎች ጥናትና ምርምር እንደ ክልል እንዲያካሂዱ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በቅርበት አብሮ እየሰራ ነው፡፡ ዩኒቨርስቲዎች የአሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች መከላከል ግብረ ሀይል አባል እንዲሆኑ የተደረጉትም ለጥናትና ምርምር ስራዎች ልህቀት ስላላቸው በዚህ ዙሪያ እንዲያግዙ ነው፡፡ አሁን ላይ ዩኒቨርስቲዎች የጀመሩት ጥናት ባይኖርም በቅድመ ጥናትና ምርምር ዝግጅት ሂደቶች ዙሪያ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አለ፡፡ ባለፈው አመት ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ጥናቱን ሊጀምር ጫፍ ላይ ደርሶ የነበር ቢሆንም በክልሉ በተፈጠረው የሰላም እጦት እንዲህ አይነት ጥናቱን ማካሄድ አልተቻለም፡፡ ወደ ፊትም ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ አካላት ከመጡ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አብሮ ለመስራት ዝግጁ ነው ብለዋል።

ሌላው የመፍትሄ አካል ተደርጎ እየተሰራበት እንደሆነ ዘርዝር አድርገው ያብራሩት ጉዳይ የወጣቶች የስብዕና ልማት ማዕከሎችና የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎችን ማስፋፋት ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ 500 ያህል ማዕከላት ያሉ ቢሆንም አገልግሎት እየሰጡ ያሉት 279 ያህሉ ናቸው፡፡ ማዕከላቱ ካላቸው የአገልግሎት ስታንዳርድ አንፃር ሞዴል፣ሁለገብ፣መካከለኛና አነስተኛ ተብለው ተለይተዋል፡፡ ማዕከላቱ በእነዚህ ስታንዳርድ አይነቶች የተመደቡት 16 አገልግሎቶች ተወስደው ነው። በዚህ መሰረት ሞዴል የሚባለው 16 አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ ከ16ቱ ስምንትና በላይ አገልግሎቶችን የሚሰጠው ሁለገብ ይባላል፡፡ መካከለኛ ደረጃ ያለው ከአራት እስከ ስድስት የሚሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን አነስተኛ የሚባለው ደግሞ በትንሹ ከሶስት እስከ አምስት አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ ከነዚህ ስታንዳርዶች አንፃር አሁን ላይ በክልሉ ያሉት ማዕከሎች አነስተኛ ተብሎ ስታንዳርድ የተሰጠውን ያህል እንኳን የሚያሟሉ አይደሉም፡፡ ማዕከላቱን በእነዚህ ስታንዳርድ አይነቶች ለመመደብ ከተለዩት 16 አገልግሎቶች መካከል ጥቂቶቹ አይሲቲ መረጃ ማዕከል፣ የኪነ-ጥበብ፣ የአመለካከት ስልጠና ግንባታ፣የስነ-ልቦና ምክር፣ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት፣ ወዘተ.የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ በማዕከሎች ውስጥ 16ቱም አገልግሎቶች ሊገኝ የሚገባ ቢሆንም በክልሉ አሉ ተብለው ቀደም ሲል የተጠቀሱት ማዕከሎች ሁሉንም አገልግሎቶች አሟልቶ የመስጠት ክፍተት አለባቸው፡፡ ሻይ ቡና እና የቤት ውስጥ ጨዋታ የሚባሉትን ፑል፣ ካራንቡላ ከመስጠት ያለፈ ሌሎች ወሳኝ የሆኑትን የስነ ልቦና ማማከር፣ የስነ ተዋልዶ ጤና እና የፈጠራ አገልግሎቶችን አይሰጡም። ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ



ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በከፊል(ባህር ዳር አለማቀፍ ስታዲዮም)

ባለፈው ዓመት ከአብክመ በጦርነት ተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባጻ ፈንድ ጽ/ቤት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ 17 ማዕከሎችን ለመገንባት እቅዶ ዘጠኝ ያህሉ ተገንብተዋል፡፡ ማዕከሎች በምስራቅ አማራ ዞኖች የሚገኙ ሲሆን በህወሀት ጦርነት ወቅት ፈራርሰዉ ስለነበር መልሶ የመገንባት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ ዓመት እነዚህ ማዕከላት በቁሳቁስ የተሟሉ እንዲሆኑና አገልግሎት እንዲሰጡ የቁሳቁስ ግዥ እየተፈፀመ ነው፡፡ ወጣቶችና ታዳጊዎች በተቻለ መጠን ክህሎቶቻቸዉን ማዳበር እንዲችሉ ሆነዉ ይሟላሉ፡፡ በጥቅሉ ማዕከላት በየአካባቢዉ እንዲስፋፉ የማድረግ ስራዎች በቢሮው እየተሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል።

የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከሎችና ስፖርት ማዝወተሪያ ስፍራዎች በወጣቶች ላይ አካላዊ፣አእሯዊና ስነልቦናዊ እድገት እንዲመጣ የሚያደርጉ ትልቅ ተቋም ናቸው፡፡ የትልቅነታቸውን ያህል ግን በአመራሩ ዘንድ ትኩረት እየተሰጠባቸው አይደለም፡፡ መንግስት ለማዕከላቱ የካፒታል በጀት እንዲመደብ ሲጠየቅ ለመመደብ ያለው ፍላጎት አነስተኛ ነው፡፡ ሻይ ቡና ብቻ የሚሸጥባቸው አድርጎ የማየት የተዛባ ግንዛቤ አለ፡፡ እንዲህ አይነቱን የተንሸዋረረ እይታ ለማስተካከል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አመራሩ እውቅና እንዲኖረው ቀርቦ የማስገንዘብ እና የማሳመን ክፍተት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ የመጣ በመሆኑ ይህ እንዲስተካከል ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ ማዕከላቱ ወጣቶች እየተዝናኑ እውቀት የሚገበዩባቸው፣ ክህሎቶቻቸውን የሚያዳብሩባቸው ተቋማት በመሆናቸው ወደፊት የወጣቶችን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች መቅረፍ የሚቻለው ተቋማቱን በስታንዳርዳቸው መሠረት ቢያንስ በትላልቅ የክልሉ ከተሞች አንድ እንዲኖርና እንዲሟሉ ማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ መረባረብ ያስፈልጋል በማለት ማዕከላቱን በማስፋፋት ሂደት ተግዳሮት ናቸው ያሏቸውን አብራርተዋል።

ከላይ የተገለፁት ማዕከላት ወጣቶችና ታዳጊዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ቀድሞ መከላከልን ታላሚ አድርገው አገልግሎቶችን የሚሰጡ ናቸው። ከእነዚህ በአላማና በሚሰጡት አገልግሎት ለየት ያለ መልክ ያላቸው ሌላ ተቋማት አሁንም ያስፈልጋሉ ብለዋል፡፡ ጫትን በመሰለ አደንዛዥ እፅ በርካታ የክልሉ ወጣቶች አደገኛ ሱስ ውስጥ ገብተው የመፍትሄ ያለህ እያሉ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ወጣቶች ታክመው መልካም ዜጋ ሆነው ወደ ቀደመ ሰብዕናቸው፣ ስነ-ልቦናቸውና ማህበረሰባቸው መመለስ እንዲችሉ ተኝተው የሚታከሙባቸው ተስማሚ የሆኑ የማገገሚያ ማዕከላት ሊኖሩ ይገባል፡፡ በተበታተነ ሁኔታም ቢሆን ደብረታቦር ዩኒቨርስቲ ከደብረታቦር ሆስፒታል ጋር በመተባበር እንዲሁም ደሴ ሆስፒታል በሱስ የተጎዱ ወጣቶችን የማገገሚያ ህክምና እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ውጭ የሚሰጡት አገልግሎቶች በዩኒቨርስቲዎችና በትምህርት ቤቶች አካባቢ ቀላል ምክር በመስጠት በጣም ያልተጎዱ ወጣቶችን ወደ ቀደመ አቋማቸው የሚመልሱ ናቸው፡፡ እነዚህ እንደ ክልል ያለውን ጅምር የማገገም ህክምና ለማሳየት ለአብነት ያህል ተጠቀሱ እንጂ በተደራጀ ማዕከል የተሰጡ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ወደፊት በክልል ደረጃ ቢያንስ አንድ በአግባቡ የተደራጀ የማገገሚያ ማዕከል መቋቋም አለበት፡፡ ይህ ጉዳይ ለክልሉ መንግስት ተደጋግሞ የቅበ ቢሆንም በበጀት ምክንያት ጥያቄው እየታጠፈ ማዕከሉን መገንባት አልተቻለም። ከላይ በተጠቀሱት ሆስፒታሎች በተሰሩት የማገገም ስራዎች እስካሁን ድረስ 164 የሚሆኑ ወጣቶች አገግመው ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀላቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሱስ ከተለከፉና ህክምና ከሚያስፈልጋቸው አያሌ የክልሉ ወጣቶች አንፃር ይህ ቁጥር "አባይን በጭልፋ" እንደሚባለው መሆኑን ጠቁመው በዚህ ዙሪያ እጅግ ብዙ መስራት እንዳለበት አሳስበዋል።

የሱስ ማገገሚያ ማዕከላትን ማስፋፋት እንደ አንድ መፍትሄ የሚወሰድ ቢሆንም አስቀድሞ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት አይሻልም ወይ? በዚህ ዙሪያ ምን እየሰራችሁ ነው የሚለው ሌላው ያቀረብንላቸው ጥያቄ ነበር። እሳቸውም ሲያብራሩ ማዕከላትን ከማስፋፋት ባሻገር መቅደም ያለበት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ላይ መስራት ነው ፡፡አመለካከቱ ያልተለወጠ ወጣት ማዕከላትን በማስፋፋት ብቻ አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች እያደረሱት ያለዉን ሁለንተናዊ ጉዳት መከላከል አይቻልም፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ በወጣቶችና ታዳጊዎች ላይ የሚደርሰው ጉዳት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ማህበረሰቡን ስለሚነካ የግንዛቤ ማስጨበ-ጫ ስራው ማህበረሰቡንም እንደሚያካትት ነው። በመሆኑም የአመለካካት ለውጥ የሚያመጡ የግንዛበቤ ማስጨበጫ ስራዎች በእቅድ እየተመሩ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መከናወን አለባቸዉ፡፡ ይህ ስራ የሚሰራዉ በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ብቻ ሳይሆን ለዚሁ አላማ ተብሎ በርካታ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን አቅፎ በተቋቋመው "አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች መከላከል ግበረ-ሀይል" የሚል ስያሜ በተሰጠው አካል ጭምር ነው፡፡ የግንዛቤ ማስቀመጫ ስራዎች ሲሰሩ ከእቅድ ማቀድ



ከአደንዛዥ እጾች አንዱ በሆነው ጫት ሱስ የተጎሳቆለ ሰው ምስል በከፊል

የሚጀምር ሲሆን መረጃዉ ከሁሉም የግብረ ሀይሉ አባላት መጥቶ የጋራ ስትራቴጅክ እቅድና አመታዊ እቅድ ይዘጋጃል፡፡ በዚህ እቅድ ውስጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝርዝር ተግባራት ተለይተው ይቀመጣሉ፡፡ ተግባራቱን ለመፈጸም እንደ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶች ተደርገው የተመረጡትን የፊት ለፊት ውይይት መድረኮችን፣ሚዲያዎችን፣እንደ በራሪ ወረቀት፣መጽሄት፣ወዘተ. የመሰሉ የህትመት ውጤቶችን በመጠቀም ይሰራል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራው የትኩረት ይዘቶች ወጣቶችና ታዳጊዎች ከአሉታዊ ልማዶችና አደንዛዥ እጾች እንዲርቁና ወደ ሱስ እንዳይገቡ የሚመክሩ፣ በጤና፣በኢኮኖሚና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚደርስባቸውን ጉዳት የሚያሳዩ፣ማህበረሰቡ፣ ወጣቶችና ታዳጊዎች ማዕከላትን በማስፋፋት ችግሩን መከላከል ላይ ትኩረት አድርገዉ እንዲሰሩ የሚቀሰቅሱ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በራሱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዉን ሲሰራ አልፎ አልፎ ከሚያመቻቸው የፊት ለፊት መድረኮችና በውስን ጊዜና መጠን ከሚያሳትማቸው የህትመት ውጤቶቸ ባሻገር ሚዲያዎችን በመጠቀም መላ ክልሉን ተደራሽ በማድረግ አብዛኛውን ወጣትና ታዳጊ እንዲሁም ማህበረሰቡን በግንዛቤ ማስጨበጫ አስተምሮት ማንቃት በኩል ክፍተቶች አሉበት።

አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን እና አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ያሉ የሚዲያና ተግባቦት ተቋማት ወጣቶችን ፣ ታዳጊዎችንና ህዝቡን ተደራሽ የማድረግ ሰፊ እድል ስላላቸው ክልላዊ ይዘት ያለው ዶክመታሪ በበጀትም በባለሙያም ድጋፍ አድርገው እንዲያዘጋጁ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እየተነጋገረና አብሮ ለመስራት ጥረት እያደረገ ነው፡፡ ዶክመንታሪው ሱስ ውስጥ ገብተው ችግር ላይ የወደቁ፣ ከሱስ ያገገሙ፣ በቁማር ጭዋታዎች ዙሪያ፣ ከአሉታዊ መጤ ልማዶች ጋር በተያያዘ፣ ወዘተ. ይዘቶች ዙሪያ ዶክመንታሪ ስራ ተሰርቶ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በማሳየት ግንዛቤ ማስጨበጥ ይቻላል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዉ እንደ ክልል ካለዉ የችግሩ አሳሳቢነት አኳያ ወደ ዞን፣ወረዳና፣ ቀበሌ ድረስ ወርዶ መስራት ላይ ክፍተት አለ፡፡ የክፍተቱ መንስኤ ምንም ይሁን ምን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዉ አብዛኛውን ወጣት ተደራሽ አድርጎ በአመለካከት መገንባት እንዲችል ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል ብለዋል።

የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ከተሰራ ምን ለውጥ እንደመጣ ወይም እንደተመዘገበ መጠየቁ አይቀሬ ነው። ይህን አስመልክቶ አቶ ደሳለኝ በሚከተለው መልኩ አስተያየታቸውን ገልፀዋል። "ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እና ግብረ-ሀይሉ የግንዛቤ ማስጨበጥ ባካሄደባቸው የክልሉ አካባቢዎች የመጡ ለውጦች ይኖራሉ፡፡ ለውጥ እንዲመጣ አብዛኛውን ወጣት ቀበሌ ድረስ ወርዶ በማግኘት ፊት ለፊት እየተወያዩ ክህሎቱን፣ዕውቀቱንና አመለካከቱን እያሳደገ የችግሩን አሳሳቢነት መገንዘብና መጨበጥ አለበት፡፡ ይህን ከማድረግ አንፃር የበጀትም ይሁን ሌሎች ተግዳሮች ቢኖሩም በተሰራው ልክ በጥቂት አካባቢዎች የታዩ ለውጦች አሉ፡፡ ለአብነት ያህል በባህር ዳር ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች የተከሉትን ጫት በመንቀል መሬታቸውን በእህል፣አትክልትና ፍራፍሬ እንዲያለሙ ሆነዋል፡፡ ይህ ግንዛቤ ያመጣው ውጤት በመሆኑ በዶክመንታሪ ተዘጋጅቶ ሌሎች አርሶ አደሮች እንዲማሩበት ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ እንደ ክልል የተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ በተበታተነ መልኩ የተፈጸመ ከመሆኑ በተጨማሪ መረጃው በትክክል ተደራጅቶ የተያዘበት አሰራር ክፍተት ስላለበት በወጣቶችና ታዳጊዎች እንዲሁም በማህበረሰቡ ላይ የመጣውን ለውጥ በአይነታዊም ሆነ በመጠናዊ ሰፋ አድርጎ ማሳየት እንደማይቻል አስታውቀዋል።

አቶ ዳሳለኝ ያነሱት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ወጣቶችንና ታደጊዎችን የማትረፍ ጉዳይ ለመንግስት ብቻ የተተወ ስራ አድርጎ የማየት የተዛባ አመለካከት በመኖሩ መስተካከል እንዳለበት ነው። በዚህ ሁኔታ ለውጥ ማምጣት ስለማይቻል ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ድርጅት፣ ወዘተ. ሃላፊነት እንዳለበት አውቆ ወጣቶችና ታዳጊዎች ከችግሩ አዙሪት እንዲወጡ ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የሃይማኖት ተቋማት ወጣቶችና ወላጆች ላይ ጥሩ ስራ እየሰሩ ነው፡፡



ከወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከሎች በከፊል(ቲሊሊ ከተማ)

የሃይማኖቶች አስተምሮት ወጣ ያሉና ከእምነቶች ጋር የሚጋጩ ልማዶችን መተግበርና አደንዛዥ እፆችን መጠቀም፤ ተጠቂ መሆን፣ መጥፎ ስነ-ምግባር መላበስ፣ ወዘተ. ስለሚያወገዝ ወጣቶችን አስተምሮና ገስጾ የመመለስ ተሰሚነት አላቸው። ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ከወጣቶች ውጭ ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች መድረስ የሚቻለው በሃይማኖት ተቋማት አማካኝነት ስለሆነ አበክረው እንዲያስተምሩ በቅርበት አብሮ መስራትና ማገዝ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ወጣቶችንና ታዳጊዎችን  ከአሉታዊ መጤ ልማዶች እና አደንዛዥ እፆች የመከላከል ሀላፊነት የመንግስት ብቻ አለመሆኑን ተገንዝበው ሲሰሩ የነበሩ የተወሰኑ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ለምሳሌ ቅድስት ምድርህን አድን ማዕከላትን በመደገፍ ይሳተፉ ነበር (አሁን ላይ ጊዜውን ጨርሶ ወጥቷል)፡፡ ወደፊት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ለመስራት ፍላጎት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከመጡ አብሮ ለመስራት ቢሮው በሩ ክፍት ነው ብለዋል ፡፡

በመጨረሻም አሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እፆች በወጣቶችና ታዳጊዎች ላይ የሚያደርሱትን ሁለንተናዊ ጉዳት ለመከላከል እንደ ተግዳሮት ወይም እንቅፋት ተደርገው የሚጠቀሱ ጉዳዮችን እንዲነግሩን ነበር የጠየቅናችው። ምላሻቸውንም የጀመሩት በጉዳቱ አሳሳቢነትና አደገኛነት መግባባት ላይ መድረስ አለመቻልን እንደ አንድ ተግዳሮት በመምዘዝ ነው። ይህን ሲያብራሩ ወጣቶችን ከጉዳቱ የመከላከል ስራ በአንድ ግለሰብ ፣ በአንድ ቢሮ ወይም በመንግስት ብቻ የሚሰራ ወይም የሚፈታ ችግር ሳይሆን ግለሰብ ፣ ቤተሰብ ፣ ማህበረሰብ ፣ ተቋማት ፣ መንግስት ፣ አገር፣ወዘተ. ሁሉም ተረባርቦ መከላከል እንዳለበት መግባባት ላይ መድረስ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ሌላው ተግዳሮት ሆኗል ብለው ያነሱት ጉዳይ አቅርቦትን ነው። ለዚህ እንደ ማሳያ ያቀረቡት ጫትን ነው። ጫት በተመጣጣኝ ዋጋና በበቂ ሁኔታ አቅርቦት ስላለው ወጣቶች በቀላሉ ፍላጎታቸውን ለማርካት ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል፡፡ የሶሻል ሚድያ መስፋፋትና የተለያዩ ፕሮግራሞች መበራከት ወጣቶችና ታዳጊዎች ሸቀለቀሉ አሉታዊ መጤ ልማዶችን የማየትና የማግኘት እድል ስላላቸው ይህም ሌላው ተግዳሮት ሁኖ ይጠቀሳል፡፡ ከዚህ ተጠየቅ በመነሳት አደንዛዥ እጾችና አሉታዊ መጤ ልማዶች ለወጣቶችና ታዳጊዎች ቅርበታቸው የመነመነ ወይም ደግሞ እሩቅ እንዲሆኑ ጠንከር ያሉ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው አጥብቀው መክረዋል።

የህግ ክፍተት መኖር ሌላዉ ተግዳሮት መሆኑን ጠቁመው ወጣቶች ተጠያቂ እንደማይሆኑ ስለሚያዉቁት አሉታዊ መጤ ልምዶችን እንደፈለጉ ሲፈፅሟቸዉ ይስተዋላል፡፡ ከአደንዛዥ እፅ ጋር በተያየዘም ጫትን በየመንገዱና በየመኪናዉ ሲቃም በህግ የሚያስጠይቅ አሰራር ስላልተዘረጋ ወጣቶች የመፈፀምና ወደ ሱስ የመግባት መጥፎ እድላቸዉ እንዲሰፋ ሆኗል፡፡ ጫት የሚያለሙ አርሶ አደሮችን ከመሬት አጠቃቀም ጋር ተያይዞ አስተማሪ ህግ ሊኖር ይገባል፡፡ የጫት መሬታቸውን በመንጠቅ እህል፣አትክልት ፍራፍሬ ለሚያለሙ አርሶ አደሮች እንዲሰጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ ወደፊት የዛሬ አገር ተረካቢ እና የነገ አገር ገንቢ  ወጣቶችና ታዳጊዎች የምንጨነቅ ከሆነ ክልሉ ይህን ሁሉ የሚከለክል ህግ ሊያወጣ ይገባዋል፡፡ መቼም ጫት ተሸጦ የሚገኘው ገንዘብ ከትዉልድ (ሰው) አይበልጥም፡፡

“በእንቁላሉ በቀጣሽኝ” እንደሚባለው አሉታዊ መጤ ልማዶችንና አደንዛዥ እፆችን ገና በእንጭጩ የሚከላከል ህጋዊ አሰራር ባለመኖሩ ዲጅታል የሆነ በቴክኖሎጅ የተደገፈ ዘመናዊ የቁማር ጨዋታ (የውሻ ውድድር ፣ የፈረስ ውድድር፣ወዘተ.) በየከተሞች እንደ አዲስ ተስፋፋቶ  ወጣቶች ከወላጆቻቸው ከጓደኞቻቸው ፣ ከወገኖቻቸው ብዙ ገንዘብ እየተበደሩ ፣ እየሰረቁ ፣ ወዘተ ለቁማር ጨዋታዎች እያዋሉ ከባድ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ እየተፈጠረ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ቀውስ ምክንያት ክልሉ ከልካይ ህግ እንዲያወጣ የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለክልሉ ምክር ቤት ብዙ ጊዜ መነሻ የሆኑ አሳማኝ ሀሳቦችን ያቀረበ ቢሆንም ምክር ቤቱ ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጠው ባለመቻሉ ሀዘን በተቀላቀለበት ስሜት ነግረውን ገለጻቸውን ቋጭተዋል፡

እኛም አሉታዊ መጤ ልማዶች አደንዛዥ እፆች በወጣቶችና ታዳጊዎች ላይ የሚያደርሱትን ሁለንተናዊ ጉዳት ፣ ወጣቶችንና ታዳጊዎችን ከጉዳቱ ለመዳንና ለመከላከል እንደ ክልል ማን ምን እየሰራ እንደሆነ ፣ ጉዳቱ ያለበት ሁኔታ ፣ የተጎጅ ወጣቶች መጨረሻ ምን እንደሚመስል ፣ መውጫ መንገዶች ምን እንደሆኑ የዳሰሰንበትን ጥንቅር በዚህ ፈፀምን —ሰላም!!

# ዲጅታላይዜሽን

በሳሮን ስማቸው

ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች ቴክኖሎጂ የሚለውን ቃል ሲጠሩ ሰምተው ይሆናል። ለመሆኑ ቴክኖሎጂ ምንድነው? ሳይንስ ወይም እውቀት የሰው ልጅ ያጋጠመውን ችግሮች ለመፍታት ወይም ጠቃሚ መሳሪያዎችን ለመፍጠር ተግባራዊ ሲሆን ቴክኖሎጂ ይባላል።

ለምሳሌ በድሮ ጊዜ የመጀመሪያው ቪላ ከድንጋይ ሲሰራ ቴክኖሎጂ ነው፥ በተጨማሪም ኢንተርኔት፣ ላፕቶፕ፣ ሮቦት፣ ካሜራ ወዘተ ባሁኑ ጊዜ የምንጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች ናቸው።

ሌላው አብዛኛውን ጊዜ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚሉት ቃላት አንዱ አንዱን በመተካት በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል። ሆኖም ግን በጥልቀት ሲታይ ሁለቱ ቃላት የተለያየ ግብና ትርጓሜ አላቸው። የሳይንስ ግብ እውቀትን ለማግኘት ሲባል ብቻ የሚከናወን እውቀትን የመፈለጊያ ሂደት ሲሆን የቴክኖሎጂ ግብ ደግሞ የሰው ልጆችን ችግሮች በመፍታት የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ የሚያደርጉ ምርቶችን መፍጠር መቻል ነው። ስለዚህ «ሳይንስ የቴክኖሎጂ ፅንስ ሲሆን ውልደቱ ደግሞ ቴክኖሎጂ» ነው። በሌላ አገላለፅ «ሳይንስ ማወቅ ሲሆን ቴክኖሎጂ መስራት» ነው። ያለ ሳይንስ ቴክኖሎጂን ማሰብ ወይም ያለ ቴክኖሎጂ ሳይንስ ላይ ብቻ ማተኮር ውጤት አልባ ነው። በመሆኑም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው የማይነጣጠሉ ፅንሰ-ሃሳቦች ናቸው።

ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለአንድ ሀገር ልማት ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። መንደሮች ወደ ትናንሽ ከተሞች፣ በኋላም ወደ ትላልቅ ከተማነት የሚለወጡት በሂደት በሚመጣው የሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ነው። ከገጠሬነት ወደ ከተሜነት የሚደረገው ሽግግር በራሱ የሚሳካው በሳይንስና ቴክኖሎጂው አተገባበር ልክ ነው። መብራት፣ የቧንቧ ውሃ፣ የተሻለ መንገድ፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች የመሰረተ-ልማት አውታሮች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስኬትን ተከትለው የሚመጡ ለውጦች ናቸው። ከእነዚህ ለውጦች ጎን ለጎን የጎለበተ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶችን ያሻሽላል። ለአብነት ያህል ምርትን ከተባይ ከመጠበቅ ጀምሮ ዝቅተኛ ተረፈ ምርት ወዳለው የምግብ ማምረት ሒደት ለማሸጋገር፣ ከጨቅላዎች እንክብካቤና በህፃናት በኩል የአካባቢ ብክለትን ከመቀነስ ወደ ንፁህና አረንጓዴ አካባቢን ለመፍጠር፣ ከመሰረታዊ ኤሌክትሪክ ፍጆታ ወደ ተሻለና ተመጣጣኝ የኮሙኒኬሽንና ትራንስፖርት ሲስተም መሸጋገር፣ ወዘተ. የሚደረግ ሽግግር ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ውጭ ሊታሰብ አይችልም። ሳይንስና ቴክኖሎጂ የዘመናዊ ማህበረሰብ ቁልፍ መገለጫም ጭምር ነው።

ማህበረሰቡ ከዘርፉ ሀሳቦችና ቁሶች ጋር ተቆራኝቷል። የስራ ቦታዎችና ሌሎች የህዝቡ መኖሪያዎች በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ቁጥጥር ስር ናቸው። በአሁኑ ዘመን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀት ያለው ሰው ዋጋው ከፍ ያለና በላቀ ሁኔታ ተመራጭ ነው። ለአብነት ያህል የኮምፒውተር ቴክኖሎጂን ብንመለከት በ1930ዎቹ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጠር ጠቀሜታው ከሂሳብ ካልኩሌተር እና ሰነድን ከመያዝ አልፎ ማንኛውንም ስራ መስራት ከሚቻልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል ተብሎ አልተገመተም ነበር። ኮምፒውተሮችም ከማንነታችን ጋር ተቆራኝተዋል፤ ዛሬ በየትኛውም የስራ ቦታ የግዴታ ያህል አስፈላጊ ሆነዋል። ድህነት በቴክኖሎጂ እድገት ይወገዳልን?

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚሊኒየም ፕሮጀክት በ2006 እ.ኤ.አ. በኒውዮርክ በዋና ፀሀፊው በተመራው የልማት ቡድን ድጋፍ ባገኘው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፕሮጀክት ላይ ታዳጊ ሀገራት ከድህነት አረንቋ ለመውጣት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ብቸኛው አማራጭ እንደሆነ አስቀምጧል። ያደጉት ሀገራት ለማደግና ከችግራቸው ለመውጣት በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ላይ የሰሩት ስራ በታዳጊ ሀገራት ላይም መተግበር እንዳለበት አቋም ተወስዷል። ቴክኖሎጂ ሀብትን በመፍጠር፣ የህይወትን የጥራት ደረጃ በማሻሻል ረገድ ብሎም ለትክክለኛ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን በኢንዱስትሪ አብዮት የሚጨበጥ ለውጥ ያመጡት ዩናይትድ ኪንግደምና ፈረንሳይ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ግብርናን ትከተል የነበረችው አሜሪካ ወደ ኢንዱስትሪው ልዕለ-ሀያልነት የተሸጋገረችበትን ለውጥ፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ወደ ኢንዱስትሪያዊ ስኬት የተሸጋገሩትን ታይዋንና ኮሪያ፣ በቅርቡም ቻይና በማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም ህንድ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪውን የሚመሩበትን ሁኔታ በማሳያነት ማንሳት ይቻላል። የእነዚህ ሀገራት ስኬት የመጣው በጥንቃቄ የተነደፈውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጅ መሰረት አድርጎ ነው። ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጪ ያለች ሀገር እንደ ኋላ ቀርና እንዳላደገች ትቆጠራለች። በየትኛውም አቅጣጫ ያለ የሰው ልጆች ምቾትና ስኬት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ጋር የተቆራኘ ነው። ኤሌክትሪክ፣ አውሮፕላን፣ ስልክ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር፣ … ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጪ ሊታሰቡ የማይችሉ ናቸው። በእነዚህ የሳይንስና ቴክኖሎጂ አካባቢዎች ደካማ የሆነች አንዲት ሀገር ዜጎቿን ለመታደግ ስትል በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆኗ አይቀሬ ነው። እንደ አሜሪካ፣ ጀርመንና ፈረንሳይ ያሉ ያደጉ ሀገራትን የዓለማችን ሀያላን ያደረጋቸው ለሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ የሰጡት ትኩረት ነው። በአሁን ጊዜ ሀገራት ያደጉና ያላደጉ ተብለው

ሲከፈሉ ዋነኛው መስፈርት ኢኮኖሚውና የሳይንስና ቴክኖሎጂው ትግበራ ነው።

ልብ ብለን ካስተዋልነው በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ የተሻለ መሰረት ያላቸው ሀገራት በፍጥነት ያድጋሉ። እንደማሳያነትም ሩሲያ፣ ጃፓን፣ ብራዚል፣ ቻይና፣ ህንድ እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። እንደ ዓለም ባንክ መረጃ እ.ኤ.አ በ2020 በዓለማችን ላይ የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ይሆናሉ ብሎ የጠቀሳቸው ሀገራት ቻይና፣ ጃፓን፣ ህንድ፣ ታይላንድ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ታይዋን ናቸው። ከጥቂት አስርት ዓመታት በፊት እነዚህ ሀገራት የሚታወቁት በነበሯቸው ደካማ ፖሊሲዎች፣ ዝቅተኛ የስራ ስነ-ምግባር እና ድህነት ነበር። በኋላም ሳይንስና ቴክኖሎጂዎችን ውጤታማ በሆነና በተገቢው መልኩ በማስተዋወቃቸውና በመተግበራቸው ፈጣን እድገት ሊያስመዘግቡ ችለዋል። እንደ ህንድ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ታይዋን ያሉ የእስያ ሀገራት ይህንኑ መንገድ ተከትለው በማደጋቸው ለሌሎች ታዳጊ ሀገራትም ጭምር ምሳሌ ለመሆን በቅተዋል።

በምጣኔ ሀብታዊ እድገታቸው የበለፀጉት ሀገራት (ምዕራባውያን) ከአጠቃላይ አመታዊ ገቢያቸው እስከ 10 በመቶ የሚሆነውን ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ስርፀት የሚያውሉበት አጋጣሚ አለ፤ እንደ ደቡብ ኮሪያ ያሉ የእስያ ሀገራትም በተመሳሳይ መልኩ ከፍተኛ በጀት ይመድባሉ። በዓለማችን ላይ ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውና ተገቢውን በጀት መድበው የሰሩ ሀገራት ዛሬ የደረሱበት ደረጃ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ፋይዳ ጋር በተያያዘ ብዙ የሚነግረን ነገር አለ። እንደማሳያነትም ለሳይንስና ቴክኖሎጂው ከፍተኛ በጀት የሚመድቡትን ሀገራት ብናነሳ እውነታውን ይበልጥ ያስረዳል።

እስራኤል ከአጠቃላይ አመታዊ ገቢዋ ውስጥ ከአራት ነጥብ ሁለት በመቶ በላይ ያህሉን ለዘርፉ በመመደብ ቀዳሚዋ ሀገር ናት። ደቡብ ኮሪያ 3.74፣ ጃፓን 3.67፣ ስዊድን 3.3፣ ፊንላንድ 3.1፣ አሜሪካ 2.7፣ ጀርመን 2.3 በመቶና ከዚህ በላይ በመበጀት በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል። የዘርፉን ስኬት ለማሳየትም በምርምርና ስርፀት ላይ ከፍተኛ ስራ የሚሰሩት ጃፓንና አሜሪካ እንዲሁም ዘርፉን በዝቅተኛ ደረጃ እየሰሩበት የነበሩትን እንደ ኔፓል ያሉ ሀገራትን በማሳያነት በማንሳት አሁን የደረሱበት የእድገት ልዩነት በማሳያነት ሊጠቀስ ይችላል።

ከአፍሪካ ሀገራት ጋር በተያያዘ የሚነሳው አንዱና ዋነኛው ችግር ለዘርፉ ከሚመደበው በጀት ጋር የተያያዘ ነው። በአብዛኞቹ ሀገራቱ ውስጥ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚመደበው በጀት ከአንድ በመቶ በታች ነው። ለማሳያነት በፈጠራው በኩል ያለውን ንፅፅሮሽ ብናነሳ፣ የዓለም አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ባለስልጣን ከአስር ዓመት በፊት ባወጣው መረጃ መሰረት እ.ኤ.አ. ከ1985 እስከ 2006 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ 882,715 የፈጠራ ማመልከቻዎች በቻይና፣ 5,220,327 በአሜሪካ የተመዘገቡ ሲሆን አፍሪካዊቷ ናይጄሪያ ግን ማስመዝገብ የቻለችው 699 ብቻ ነበር። ይህ ውጤትም በኋላ ላይ ለነደፈችውና በቀጣይነት ለምናነሳው ስትራቴጂ እንደ አንዱ የማንቂያ ደወል የሚወሰድ ነው።

ናይጄሪያ ቀድማ ከነበረችበት ሁኔታ ለመውጣት በሳይንስና ቴክኖሎጂው ላይ “የማይቀለበስ” ያለችውን አብዮት የጀመረችው ቀደም ብላ ነው። ናይጄሪያ እ.ኤ.አ. በ2020 ለሰነቀችው ከበለፀጉት የዓለም ሀገራት ተርታ የመሰለፍ ራዕይም ሳይንስና ቴክኖሎጂው የማይተካ ሚና በመጫወት ልማቷን እንደሚያፋጥንላት አምናለች። ኢንጂነሮቿና ሳይንቲስቶቿም የሚጠብቃትን ፈተና እንዲወጡላት እየተጋች ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የዘርፉ ምሁራን ከሚጠቁሙት መፍትሔ አንዱ ብሔራዊ የሳይንስ ፋውንዴሽን በማቋቋም ቢያንስ ከሀገሪቱ አመታዊ ገቢ ከ2 በመቶ የማያንሰው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ መዋል አለበት የሚል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች ላይ ለሳይንስ ትምህርት ትኩረት (ከ80-90 በመቶ) በመስጠት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስርፀትን መታደግ እንደሚቻል ያወሳሉ።

የኢኮኖሚ መሰረታቸውን እንደ ነዳጅ ዘይት ባለ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጥለዋል የሚባሉት የአረብ ሀገራት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የነበራቸው አመለካከት ከቀደመው ጊዜ በፍፁም የተለየ እየሆነ መጥቷል። እ.ኤ.አ በ2012 መጋቢት ወር ላይ 22 የአረብ ሀገራት (ስምንቱ ከአፍሪካ) ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ለልማት የሚል አዲስ ስትራቴጂ ነድፈው አፅድቀዋል። ሀገራቱ የሳይንስ ትምህርትን ጥራት በማሻሻል፣ ዩኒቨርስቲዎችን በማጠናከርና በመደገፍ፣ የምርምር አቅምን በመገንባትና ዓለም ዓቀፍ ትብብርን በማበረታታት ላይ ያተኮረ አቅጣጫም አስቀምጠዋል። ከአመታዊ ገቢያቸው ውስጥ ለምርምርና ስርፀት ይመድቡት የነበረው የ0.3 በመቶ በጀትም ወደ 3 በመቶ፣ የግሉ ሴክተር አስተዋፅዖ ደግሞ ከ30 በመቶ ወደ 40 በመቶ ማደግ እንዳለበት ወስነዋል። የምሁራንን ፍልሰት መቀነስና ዩኒቨርስቲዎችንና የምርምር ተቋማትን ሳቢ ማድረግም በሀገራቱ ስትራቴጂ ላይ ከስምምነት የተደረሰባቸው ነጥቦች ናቸው። አንባቢዎቻችን በዛሬው እትማችን ልናስነብባችሁ የወደድን በሀገራችን ብሎም በክልላችን በሳይንስና ቴክኖሎጅ ዘርፍ የተሻለ ዕድገት ለማምጣት የተጀመር በርካታ ስራዎች ቢኖሮም በቅርቡ የኢትዮ ኮዶርስ በኢትዮጵያ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግስት መካከል የጋራ ተነሳሽነት የተጀመር ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም እ.ኤ.አ. በ2017 በክቡር ሼክ መሀመድ ቢን ራሺድ አል ማክቱም በአለም ኢኮኖሚ ፎረም የታወጀው ታሪካዊው የአንድ ሚሊዮን አረብ ኮድደር ፕሮግራም ተብሉ ይጠራል፡፡ ይህን ኢትዮ ኮደርስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስራና ስልጠና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ለሆኑት አቶ አማረ አለሙ ጥያቄችን አቀርብን፡፡

**ሐዲስ**፡- በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠየቅ ፈቃደኛ በመሆነውት እያመሰግን ስምዎትን የስራ ድርሻዎን ቢገልፁልኝ ?

# ልዩ ልዩ



"በስልጠና ራስን በማብቃት ተወዳዳሪነትን ማስፋት"

አቶ አማረ አለሙ

**እንግዳ፡**- አማረ አለሙ እባላለሁ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስራና ሥልጠና ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የኮደርስ ኢንሸቲቭ የቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነኝ፡፡

**ሐዲስ፡-** ለመነሻ ይሆን ዘንድ ኢትዮ ኮደርስ ኢንሸቲቭ ፕሮግራም ምንድን ነዉ? እንደ ሀገር ብሎም እንደ ክልል መቼ ተጀመረ? እንዴትስ እየተመራ ነው?

**እንግዳ፡-** በሀገራችን ብሎም በክልላችን ሀምሌ ወር 2016 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን የኢትዮጵያ ኮደርስ ፕሮግራም በኢትዮጵያ እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት የተነደፈ የዲጂታል ክህሎት ስልጠና መርሃ ግብር ነው። የመርሃ ግብሩ አላማ ወጣቱ ትውልድ በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መሳተፍ የሚያስችለውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው። ይህ ፕሮግራም የኦንላይን ኮርሶችን እና ሌሎች ደጋፊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማቅረብ እ.ኤ.አ በ2026 አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በፕሮግራሚንግ ፣ በዳታ ሳይንስ ፣ በአንድሮይድ ልማት እና አርተፊሻል ኢንተለጀንስን በዲጂታል ክህሎት መሰረታዊ እውቀትን ማስጨበጥን ላይ ግብ ያደረገ ነው።

የዲጅታል ክህሎት ስልጠና እንደ ሀገር ከሚሰለጥኑ ወጣቶች ውስጥ 767,963 የክልላችን ወጣቶችም የዚህ ፕሮጋራም ተጠቃሚና ተደራሽ መሆናቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮቻችንን እንድንቀርፍ ያስችለናል። በተለይ ወጣቶቹ በመርሃ ግብሩ በመሳተፍ በግላቸው የሚያገኙት ጥቅም እንዳለ ሆኖ የመርሃ ግብሩ ውጤታማነት ለክልላችን የዲጂታል ክህሎት ስኬት እና ተወዳዳሪነት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አለው።

**ሐዲስ፡-** ኢትዮ ኮደር አላማውና ጠቀሜታው ምንድን ነዉ? የሚሰጡ ሥልጠናዎች ምን ምን ናቸዉ?

**እንግዳ**፡- የስልጠናዎቹ የሚቀርቡት አለም አቀፍ የዲጂታል ክህሎቶችን በኦንላይን በማስተማር ስመጥር ከሆነው ከዩዳሲቲ ፕላትፎርም ጋር በመተባበር በመሆኑ እጅግ የተሳካ ያደርገዋል። ስለሆነም ፕላትፎርሙ የተለያዩ የፕሮግራሚንግ

የዌብ ልማትን እና ሌሎች በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የኮዲንግ ስልጠናዎችን ይሰጣል።

በፕላትፎርሙ የሚሰጡ ኮርሶች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው እና ከኢንዱስትሪ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው ሰልጣኞች በፕላትፎርሙ በመመዝገብ ኮርሶቹን አንላይን ይወስዳሉ። አንዱ ኮርስ እስከ 6 ሳምንት ሊወስድ ይችላል። እንደ ክልልም በኦንላይን ለየኮርሶቹ አማካሪዎች እና ውይይት የሚያደርግ የኦንላይን ኮሚኒቲ ይኖራል ኮርስ ለጨረሰ ሰልጣኝ ሰርተፊኬት ይሰጣል።

ኢትዮ ኮደርስ ኢንሸቲቭ ፕሮግራም በተመለከተ በአጠቃላይ በአገራችን big resulet strategic 2025 ተብሎ የመጣ ሲሆን የኢኮኖሚ ልማትን ለማረጋገጥ የሚቻለው ተብሎ ከተለዩት የትኩረት ዘርፍ መካከል ግብርና ፤ የማንፋክቸሪንግ ፤ የቱሪዝም የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚ፤ ዲጅታላይዜሽን ሲሆን ዲጂታላይዜሽን በራሱ አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ ነው፡፡ እንዴት ይመራል ለተባው በፌደራልና በክልል ደረጃ ይህን የሚያስፈፅም ቴክኒካልና አብይ ኮሚቴ ተዋቅሮ በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ አህመዲን ሞሀመድ (በዶ/ር) የተጀመረ ፕሮግራም ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ኮደርስ ኢንሸቲቭ አራት ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን እንደ አማራ ክልል በሦስት አመት ውስጥ 768 ሺህ የሚጠጉ ወጣቶች ይሳተፉበታል፡፡

የኢትዮ ኮደርስ ኢንሸቲቭ ፕሮግራም አጠቃላይ ጠቀሜታዉ የሀገራችን ብሎም የክልላችንን ወጣቶች



ኢትዩ ኮደርስ ሰልጣኞች ከፊል ገጽታ

በዲጅታል ኢኮኖሚው ውስጥ በማሳተፍ የዲጂታል ኢኮኖመሚ ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው ::

ዲጂታላይዜሽን በራሱ የኢኮኖሚ ምንጭ ነዉ፡፡ሌሎችንም ተግባራት የሚያፋጥን በመሆኑ ይህን ብቁ የሆነ ዜጋ በማዘጋጀት ኢትዮጵያ በ2025 እስትራቴጂክ እቅድ እዉን ለማድረግ የሚያስችል በ በዜሮ እና በአንድ ኮምፒዉተር የሚናገርና ሁሉን ነገር ኮች (Coch) የሚያደርግ ሰው መፍጠር ሲሆን የስራ ዕድልም ይፈጠርለታል ፤ ቴክኖሎጂን ይጠቅማል ፤ የራሱን ሥራም ይፈጥራል፡፡ ሰልጥኖ መገኘት ከኢትዮጵያ ውጭ ጭምር በኦንላይን ሥራ የሚያገኙ ወጣቶችን መፍጠር ያስችላል፡፡

**ሐዲስ፡-** ፕሮግራሙ በዋናነት ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው የትኞቹን የህብረተሰብ ክፍሎች ነው? ለምን ?

**እንግዳ፡-** ሥልጠናው በዋናነት ተጠቃሚ የሚያደርገው ወጣቶችን ሲሆን ከእነዚህም መካከል 60 በመቶ ሴቶች እንዲሆኑ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡

በተጨማሪም ከተፈቀደው ቦታ ማንኛውም መሰልጠን የሚፈልግ አካል መሰልጠን ይችላል፡፡ ለወጣቶች ቅድሚያ የተሰጠበት ምክንያት ሀገሪቱ ወደ ፊት የምትፈልገውን ስትራቴጂክ የሚመራ አካልና ረጅም ጊዜ የመስራት እድል ያለው ወጣቱ ስለሆነ ከስራ አጥ አንፃርም ስንመለከተዉ 28% ወጣቱ በመሆኑ ይህንን ኃይል ብቁ ማድረግና ሥራ እንዲፈጠርለት ማገዝ ዋናው ተግባር ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ እድሜያቸዉ 39 አመት በታች ያሉ ወጣቶች ላይ ያተኩራል፡፡

**ሐዲስ፡-**ሥልጠናው የሚሰጠው በየትኞቹ አካባቢዎች ነዉ? እነዚህ አካባቢዎች ሥልጠናውን ለመስጠት ምን ያህል ዝግጁ ናቸው?

**እንግዳ፡-** ኮደርስ ስልጠናው የሚሰጥባቸው አካባቢዎችን ለይተናል፡፡ በክልሉ በዋናነት ባህርዳር ፤ ጎንደር ፤ ደሴ እና ኮምቦልቻ መሰረት አድርጎ የሚሰጥ ቢሆንም በሁሉም የዞን ከተሞች የስልጠና ማዕከላትን ለማደራጀት ጥረት ተደርገዃል ፡፡

እነሱም 10ሩ ዩንቨርስቲዎች ፣ የመንግስት እና የግል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ፣ የመንግስት የግብርና እና የጤና ኮሌጆች፣ የወጣቶች ስብዕና ግንባታ ማዕከላት ፣ የመምህራን ኮሌጆች እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ሌሎችም ከላይ የተጠቀሱትን የስልጠና ማዕከላት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ የስልጠና ማዕከላት ይሆናሉ፡፡

በተጨማሪም ስልጠናዉ የሚሰጠው በኦንላይን ስለሆነ ኢንተርኔት ፣ ኮምፒዉተር ፣ Smart Phone access የሌላቸውን በመለየት በዩንቨርስቲዎች ፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በግብርና ኮሌጆች ፣ ጤና ቢሮዎች ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን በመጠቀም ተዘጋጅተናል፡፡ ለዚህም ደግሞ ረዳት አሰልጣኝ ኮምፒውተር የሚከፍትላቸውን አመቻችቷል፡፡

**ሐዲስ**፡- ስልጠናው በማን እና እንዴት ይሰጣል? ምን ያህል ካፒታል ተበጅቷል?

**እንግዳ፡-** ሥልጠናውን የሚሠለጥነው በራሱ ነው ፡፡ የስልጠናውን ፕሮግራም Sponser ያደረገው የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ሲሆን ሥልጠናውን የሚሰጠው Udacity የተባለ የአሜሪካ ዩንቨርስቲ ካምፓኒ ነው፡፡ ምንም እንኳን ምዝገባውም ሆነ ስልጠናው የሚከናወነው በግል ቢሆንም በጋራ ለማሰልጠንና በማእከላት ለሚሰለጥኑ ወጣቶች ረዳት አሰልጣኝ ስለሚያስፈልግ በሚከተሉት ተቋማት ውስጥ ረዳት አሰልጣኞችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ ረዳት አሰልጣኞችን ፤ ከ10ሩ ዩንቨርስቲዎች፡፡ የመንግስት እና የግል ቴክኒክ ሙያ ኮሌጆች ፣ ከመንግስት የግብርና እና የጤና ኮሌጆች ፣ ከመምህራን ኮሌጆች እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከሌሎችም የመንግስት ተቋማት ይለያሉ፡፡

**ሐዲስ**፡- ሥልጠናውን በተመለከተ ምዝገባ የሚካሄደው እንዴት ነው? ከሠልጣኞች ምን ይጠበቃል፣

**እንግዳ፡-** ምዝገባ የሚካሄደው በተናጠል በተመርጡ ማዕከላት አማካኝነት ሲሆን አምስት ሚሊዮን ኮደር ኢንሸቲቭ የኢ-ሜል አድሬስ ላይ ከፍቶ ፎርሙን ሞልተው ሲጨርሱ ሥልጠናውን መጀመር እና ኮርሶችን በመከታተል ራስን ማብቃት ይቻላል፡፡ www.ethiocoders.et ወይም www. Amharacoders .et የሚለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም በቀላሉ መመዝገብ ይቻላል፡፡

# ልዩ ልዩ




ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ የሚገኝ ዓለማቀፋዊ ፋይዳ ያለው ሰርተፍኬት

**ሐዲስ፡-** ለሥልጠናው የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች ይኖሩ ይሆን? ካሉ ቢገለፁልኝ?

**እንግዳ፡-** እንደ አማራ ክልል ለሥልጠናው ዘጠኝ መቶ የተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት የተለዩ ሲሆን ለዚህም ሶስት መቶ 14 አሠልጣኞች ተመልምለዋል፡፡

**ሐዲስ፡-** ሥልጠናውን እንደ ክልልም ሆነ እንደ ሀገር የተያዘው ዕቅድ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል? የሚሰታፉ የሠው ኃይል ዕቅድ ምን ያህል ነው?

**እንግዳ፡-** እንደ አማራ ክልል በሶስት አመት 767 ሺህ 963 ፤ በ2017 የበጀት አመት 191 ሺህ 991 የክልሎችን ወጣቶችን በፕሮግራሙ ተመዝግበው እንዲሰለጥኑ እና የማጠናቀቂያ ሰርትፊኬቶች እዲኖራቸው በማስቻል የሥራ ባለቤት እንዲሁኑ አና በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

**ሐዲስ፡-** በክልል ደረጃ አሁን ያለው እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

**እንግዳ፡-** ሥልጠናውን ለማሳካት ግንዛቤ መፍጠር ላይ እየሠራን ነው፡፡ በእዚህ ረገድ 44 ሺህ የሚደርሱ ሰልጣኞችን ማሰልጠን ችለናል፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ 23 ሺህ የሚሆኑት ስልጠናውን አጠናቀዋል፡፡

**ሐዲስ፡-** ይህንን ሥልጠና ውጤታማ ለማድረግ ኃላፊነት ወስዶ የሚሠራ ተቋም አለ? ካለ የሠራቸውን ሥራዎች ቢያብራሩልኝ ?

**እንግዳ፡-** ኃላፊነት ወስዶ የሚመራው ተቋም የለውም አገራዊ ኢንሸቲቭ ነው፡፡ አብይ ኮሜቴ አለው፡፡ በዋናነት ግን አህመዲን ሞሀመድ (ዶ/ር ) የሚመራው ሲሆን ተግባር የሚካሄደው ግን በኮሌጆች ፤ በዩንቨርስቲዎች ፤ ትምህርት ቤቶች ፤ የወጣቶች ግንባታ ማዕከላት ፤ ሲቪል ሰርቢስ ፤ የኢንቬሽንና እና ቴክኖሎጅ ፤ ፕላንና ልማት ፤ ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ናቸዉ፡፡ ስለሆነም በፌደራል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፤ ትምህርት ቤቶችን ትምህርት ቢሮ ፤ ሴቶችን በተመለከተ ሴቶች ሊግ ወጣቶችን የወጣት ሊግ ሲቪል ሰርቫንቱን ሲቪል ሰርቪስ እንደየ ተዋራዳቸው ይመራሉ፡፡

**ሐዲስ፡-** በዚህ ስልጠና ሰርተፍኬቱን አግኝተው ተጠቃሚ የሆኑ አሉ? ካሉ ቢያብራሩልን፡፡ ምን ያህል ናቸው፡፡

**እንግዳ፡-** እስካሁን ባሳለፍናቸው አጭር የስልጠና ቆይታዎች ተጠቃሚ ተብለው የተለዩ የሉንም፡፡ሆኖም ግን በቀጣይ ተትጠናክሮ የሚሰራበት ይሆናል፡፡

**ሐዲስ፡-** እንደ ክልል የተቀመጠውን የስልጠና ቁጥር ለማሳካት ምን ታስቧል?

**እንግዳ፡-** ጥንካሬው ኢንሸቲቡን ወስዶ ዕቅድ ማቀድ ፤ አደረጃጀት መፍጠር ፤ ችግሮችን ለይቶ የተኞቹ ላይ ትኩረት መደርግ ያለባቸውን ተቋማት ፤ ግለሰቦች ፤ በዕድሜ እና በአካባቢ ተለይተዋል ፡፡ አጋር አካላትን አካቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ አንፃራዊ ሰላም ባላቸው አካባቢ ወርደን ሥራውን ለማሳካት ተግተን እየሰራን ነው፡፡

**ሐዲስ:-** ስጠናው በምን ዙሪያና በምን ያክል ጊዜ ይጠናቀቃል?

**እንግዳ:-** ስልጠናው ምዝገባው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የሚሰጡ የስልጠና አይነቶችን እስከ ማጠቃለያ ድረስ ያለው ስድስት ሳምንት የሚጠብቅ ሲሆን ነገር ግን እንደ ሰው የዕውቀት አቀባበል እንጂ በ2 ሳምንት ሊጨርስ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ስድስት ሳምንት ሞልቶ ማጠቃለያ ፈተናውን ወስዶ ካላጠናቀቀ ሲስተሙ በራሱ ይዘጋል፡፡ እንደዚህ አይነት ነገር ሲያጋጥም ሰልጣኙ ስልጠናውን እንደገና ባዲስ ተመዝግቦ ይጀምራል እንጂ ካቆመበት የሚቀጥል ፕሮግራም አይደለም፡፡

**ሐዲስ:-** ስልጠናውን ለመውሰድ አስፈላጊ መስፈርቶች አሉ? ካሉ ምንድን ናቸው?

**እንግዳ:-** ስልጠናውን ለመሰልጠን ማንኛውም የኮፒውተር አውቀት ፣ እንግሊዘኛ ቋንቋ መረዳት የሚችል ኢሜል አድሬስ ያለው ይህን መስፈርት ማሟላት የሚችል በሙሉ መሰልጠን ይችላል፡፡

**ሐዲስ:-** እንደ አማራ ክልል አሁን ያለበት የአፈጻጸም ደረጃና እየተገኘ ያለው ውጤት ምን ይመስላል?

**እንግዳ:-** እንደ አማራ ክልል 205 ሺህ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ሲሆን ፣ 44 ሺህ ያህሉ ስልጠና እየወሰዱ ያሉና ፤ 23 ሺህ ደግሞ ስልጠናውን አጠናቀዋል፡፡

**ሐዲስ:-** ስልጠናውን ከመስጠት ባለፈ የስራ ዕድል ከማመቻቸት ረገድ እንደ መንግስት ምን የታሰበ ነገር አለ?

**እንግዳ**;- መንንግስት ያሰበው ወጣቶች በኦንላይን የሚለቀቁ ስራዎችን እዲወዳደሩ ከማገዝ ባለፈ ኢኮኖሚን እዲመሩ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ሰው የማዘጋጀት እና ብቁ ተወዳዳሪ የማፍራት ስራ ነው፡፡

ሌላው አለም ከማንዋል አሰራር የወጣበት ዘመን በመሆኑ ይህን የሚጠቀም ሰው ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከህሎታቸው ያደጉ ሰዎቸ ከሆኑ ሴሰተሙ ውስጥ ገብተው መወዳደር ይችላሉ፡፡ የመንግስት ድረሻ ከአለም ገበያ ጋር ተወዳድረው እዲሰሩ ማስቻል ነው፡፡

**ሐዲስ:-** እስካሁን በነበረው ስልጠና የታዩ ጥንካሬዎች እና እጥረቶች ምንድ ናቸው? እጥረቶች እዴት ተፈቱ?

**እንግዳ:-**ጥንካሬዎች ኢንሽቲቩን በመውሰድ ዕቅድ አቅደን አደረጃጀቶችን አደራጅተን ወደ ስራ መግባታችን አማራ ክልል አሁን ባለበት ሁኔታ ካለው ነባራዊ ችግር አንጻራዊ ሰላም ያለባቸው ቦታ መርጠን መለየታችን አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ክልሉ ያለበት የጸጥታ ችግር ይህን ስራ የሚጎትት ቢሆንም ከሌሉች ክልሉች ባልተናነሰ መልኩ መስራቱ ጥንካሬ ሲሆን ችግሮች ደግሞ የአመራር ትኩረት ማነስ ፣ ትኩረት ልናደርግባቸው የሚገቡ ነገሮችን አለመለየት ፣ ተቋማትን ፣ አጋር አካላትን አለማሳተፍ አሰታፌነትና የድጋፍና ክትትል ማነስ ያጋጠሙ ችግሮችን በማየት ከርዕስ መሰተዳደሩ እስከ ታች ደርሰ በመገምገም የስራ ክፍፍል በማድረግ የነበሩብትን እጥረቶች ፈተናል፡፡

**ሐዲስ:-** ለዚህ ተግባር መሳካት ከማን ምን ይጠበቃል?

**እንግዳ:-** ስራው የሚመራው በኮሜቴ ነው፡፡ ኮሜቴ የተዋቀረው ተቋሙ ለስራው አስፈላጊ ነው ተብሉ ተምኖበት ነው፡፡ ለምሳሌ ስራና ስልጠና ቢሮ በስሩ 126 የመንግስት 120 የግል ኮሌጆች 246 ተቋማት አሉት፡፡ እነዚህን በማስተባበር መደበኛ ስራ እዲሰሩ ማድረግ፡፡ አጫጭር ስልጠናዎች የሚወስዱትን ከዚህ ሰልጠና በተጨማሪ እዲሰለጥንኑ ማድረግ የአካባቢ ወጣቶች ዕድል የሌላቸው ገብተው እዲሰለጥኑ ዕድል ይሰጣል፡፡ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሬዎች ስልጠና እዲሰለጥኑ ፣ ግብረና ፣ ጤና ፣ ሴቶች ሊግ ወጣቶች ሊግ እዲሁም ሌሉችም ተቋማት በየተዋረዳቸው ጊዜ ፣ ሀብትና ጉልበት የሚቆጥብ አሰራር ማበጀት አለባቸው፡፡ ሌላው ሰይንስና ቴክኖሎጅ ትልቅ አስተዋጾ አድረጓል ሁሉም ተቋም ደርሻ ስላለው ሀሳቡን መቀበልና ማስቀጠል ነው፡፡

**ሐዲስ:-** በመጨረሻም ቀሩ የሚሉትን አሳብ ጨምረው የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ቢገልጹልን?

**እንግዳ:-** ኮደርስ ኢንሽቲብ በኮሜቴ የሚመራ የሶስት አመት ፕሮጀክት ሲሆን እንዴት ይመራ የሚለውን ክልሉ ሊያስብበት ይገባል፡፡ ይህ እስከሚመቻች ድረስ ግን የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ አብዛኛው ዜጋ የቴክኖሎጅን ፍላጓት ማሳደግ ብቻ ሳይሆን መጠቀም ማዳበር አለበት፡፡ ይህን ለማሳካት ደግሞ የተለያዩ አሰራሮች ስላሉ ለክልሉ የተሰጠውን ዕቅድ በማሳካት ዜጎችን ስራ ጠባቂ ሳይሆን ስራ ፈጣሪ ማድረግ ያስችላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እንደ አለምና እንደ ሀገር ከሚመነጨው ኢኮኖሚ የክልሉ ዜጓች ተጠቃሚ እዲሆኑ ከተፈለገ ማዘመን አለብን፡፡

በቴክኖሎጂ ለመዘመን ደግሞ ምቹ ሁኒታውችን በመፈጠር የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሟላት አመራሩ ያለውን ወሳኝ ሚና በአግባቡ መወጣት አለበት፡፡ ብልሹ አሰራሮችን አስወግዶ ቀልጣፋና የዘመነ አሰራር በመዘረጋት የክልሉን ህዝብ የሚያረካ አገልግሉት ለመስጠት በቁጥጥር ሳይሆን በሲስተም የሚመራበት አሰራር ለማስፈን ጠንክሮ መስራት እንደሚገባ በመግለጽ አሰባቸውን ቋጭተዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም አቶ አማረ አለሙ ጋር ያደርግነው ቆይታ በዚሁ ያጠናቀቅን ሲሆን ለሰጡን ማብራሪያ በጣም እያመሰገንን አንባቢዎቻችን ኢትዮ ኮደርሰ ፕሮግራም ከተጀመረ 7 ወራት ያስቆጠረና ለሀገራችን የተሰጠው የስልጠና ዕድል በቀጣይ ጥቂት ዓመታት ውሰጥ የሚጠናቀቅ በመሆኑ በተለይ ወጣቶች የዲጅታል ቴክነኖሉጅ አቅመችሁን በማጠናከር በአለም አቀፍ የውድድር ገበያ ላይ ብቁ ሆናችሁ ራሳችሁንና አገራችሁን ተጠቃሚ ታደርጉ ዘንድ እድሉን እንድትጠቀሙበት የዝግጅት ክፍሉ መልዕክቱን ያስተላለፉል፡፡ሠላም፡፡





የለማ ተፋሰስ(ደቡብ ወሎ ወረኢሉ  ወረዳ)



